ጅማ ዩኒቨርስቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ-ግብር

# ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ያለው ሚና (በ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

ማስረሻ ብዙነህ

ነሐሴ፣2016 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረው ሚና (በ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

ማስረሻ ብዙነህ

አማካሪዎች

ማንያለው አባተ (ዶ/ር)

ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ

አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ፣2016 ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ማረጋገጫ

ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረው ሚና በ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርስቲ የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር (“TeAm”) የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና ጅማ ዩኒቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ!

ስም፦ ማስረሻ ብዙነህ አለሜ

ፊርማ

ቀን

# አበርክቶ

ይህ ጥናት የአባቴን መልክ ሳየሁበት በእውነተኛ የወንድምነት ተምሳሌት የአባትነትም ድርሻን እየተወጣ ሲደግፈኝ ለነበረው ዛሬ ላይ በአካል ባይኖርም በመንፈስ እስከህይወቴ ፍጻሜ ከውስጤ ለማይለየው ለውድ ወንድሜ ሙሉጌታ ብዙነህ አለሜ መታሰቢያ ይሁንልኝ!

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን ጥናት ከጅማሬው እስከፍጻሜው እንዳከናውን ለረዳኝ አምላኬ ክብር ምስጋና ይግባው በመቀጠል ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለጥናታዊ ጽሁፌ ገንቢ አስተያየት በመስጠት ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶክተር ማንያለው አባተ ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ!

በትምህርት ቆይታዬ የምርምር ጽንሰ ሀሳቦች እና ዘዴዎችን በተመለከተ እውቀት ላስጨበጡኝ ውድ መምህሮቼ ለዶክተር እንድሪስ አባይና ለዶክተር ለማ ንጋቱ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ!

ጥናቱ ሙከራዊ ጥናት በመሆኑ ከተተኳሪዎች ጋር ብዙ ጊዜ ማሳለፍን ይጠይቅ ስለነበር ተተኳሪዎች ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ በአዲዮ ወረዳ በሜራ ቀበሌ የሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን፣ተማሪዎችና የአስተዳደር ሰራተኞች ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ!

በመጨረሻም ጥናቴን ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ እስከፍጻሜው ድረስ ከጎኔ ሆነው ሲያበረታቱኝ ለቆዩት ለውድ ቤተሰቦቼ እንዲሁም የህይወቴን ምዕራፍ ለከፈተችልኝ ለውድ ባለቤቴ ለወይዘሮ ገነት ዋሲሁን ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ!

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


.......................................................................................................i

ማረጋገጫ.......................................................................................................i

አበርክቶ .......................................................................................................ii

ምስጋና .......................................................................................................iii

አህጽሮተ ጥናት (Abstract) ......................................................................... viii

ምዕራፍ አንድ .......................................................................................................1

መግቢያ.......................................................................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ .......................................................................................................1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.......................................................................................................5

1.3 የጥናቱ መላምት.......................................................................................................6

1.4 የጥናቱ አላማ.......................................................................................................6

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ .......................................................................................................6

1.6 የጥናቱ ወሰን .......................................................................................................7

1.7 የጥናቱ ውስንነት .......................................................................................................7

ምዕራፍ ሁለት .......................................................................................................9

ክለሳ ድሳናት .......................................................................................................9

2.1 ከመጻፍ ጋር የተያያዙ የመማር ንድፈ-ሀሳቦች.......................................................................................................9

2.1.1 የጽሑፋዊ ንጽጽሮሽ ንድፈ-ሀሳብ (Contrastive Rhetoric Theory).....................9

2.1.2 የግንዛቤ እድገት ንድፈ-ሀሳብ.......................................................................................................10

2.1.3 የተግባቦታዊ ንድፈ-ሀሳብ (Communication Theory).....................................10

2.1.4 የማህበራዊ ግንባታውያን ንድፈ-ሀሳብ (Social Connstruction Theory)............11

2.2 የመፃፍ ክሂል ምንነት .......................................................................................................13

2.3 የመጻፍ ትምህርት ዓላማ.......................................................................................................15

2.4 በመጻፍ ትምህርት ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮች.......................................................................................................19

2.5 መጻፍን ማስተማሪያ መርሆዎች .......................................................................................................19

2.6 የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች ....................................................................21
2.6.1 ውጤት-ተኮር አቀራረብ (Product approach) ................................................21
2.6.1.1 የውጤት-ተኮር አቀራረብ የመጻፍ ደረጃዎች......................................................22
2.6.1.2 በውጤት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት የመምህሩ ሚና ........................................24
2.6.2 ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ምንነት ...........................................25
2.6.2.1 የሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ አስፈላጊነት ..................................28
2.6.2.2 የሂደት-ተኮር አጻጻፍ ዘዴ ቅደም-ተከተላዊ ደረጃዎች ......................................29
2.6.2.3 በሂደት-ተኮር አቀራረብ የመምህሩ ሚና..........................................................31
2.6.2.4 በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪው ሚና ............................32
2.6.2.6 በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ለተማሪዎች የሚሰጥ ምጋቤ-ምላሽ..33
2.7 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ..........................................................................................34
ምዕራፍ ሶስት ...............................................................................................................36
የአጠናን ዘዴ ..................................................................................................................36
3.1 የጥናቱ ንድፍ..........................................................................................................36
3.2 የተማሪዎችና የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ......................................................37
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ....................................................................................37
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አስተማማኝነትና ትክክለኛነት .......................................38
3.5 የቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ፈተና አስተማማኝነት ...............................................40
3.6 የማስተማሪያ ፅሁፍ አዘገጃጀት ...................................................................................40
3.7 የማስተማር ትግበራ ሂደት..........................................................................................41
3.8 የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ዘዴ...........................................................................42
3.9 የጥናቱ ስነ-ምግባራዊ ሁኔታ .......................................................................................42
ምዕራፍ አራት ................................................................................................................44
የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራርያ..........................................................................44
4.1 የመረጃ አተናተን .......................................................................................................44
4.1.1 የፈተናዎቹ የአስተማማኝነት ደረጃ........................................................................44
4.1.2 የቅድመና የድህረ-ትምህርት ፈተና መረጃ ትንተና ..............................................45

4.1.2.1 በቅድመ-ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና ....................................45
4.1.2.2 የድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት መረጃ ትንተና ..........................................46
4.2 የውጤት ትንተና ....................................................................................48
4.2.1የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በቅድመ-ትምህርት ፈተና የተገኘ ውጤት ትንተና.....................................................................................................49
4.2.2 የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና .....................50
4.2.3 የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ንጽጽር.........52
4.3 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ፡-.........................................................................54
ምዕራፍ አምስት.............................................................................................56
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት ..............................................................56
5.1 ማጠቃለያ ..........................................................................................56
5.2 መደምደሚያ ..........................................................................................57
5.3 አስተያየት ............................................................................................58
ዋቢ ጽሁፎች ..............................................................................................60
አባሪ አንድ:- ጥናቱን ለማከናወን የተዘጋጀ ሞጁል የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ..............64
በመጻፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የውጤት-ተኮር አቀራረብ ዘዴ አተገባበር .........................64
መማሪያ ክፍል ውስጥ የመጻፍ ትምህርትን በሂደት-ተኮር አቀራረብ ዘዴ.......................66
የሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ምንነትና የሂደት ደረጃዎች.........................67
የማቀድ ደረጃ.........................................................................................68
የማርቀቅ ደረጃ...........................................................................................69
የክለሳ (የድህረ-ጽህፈት) ደረጃ ........................................................................70
አባሪ ሁለት:- ለቅድመ-ትምህርት ፈተናና ለድህረ-ትምህርት ፈተና እንዲሁም ለመማር ማስተማሩ ተግባር የሚያገለግሉ ርዕሶችን ለመምረጥ ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቀርበው በደረጃ የተመረጡ ርዕሶች .......................................................................71
አባሪ ሶስት፡- የግልና የቢጤ የጽሁፍ መገምገሚያ መመሪያ.............................................71
አባሪ አራት፡- የቅድመና የድህረ-ትምህርት የመፃፍ ክሂል ፈተናዎችን ለማረም ተግባር ላይ የዋለው የነጥብ አሰጣጥ፡-.......................................................................74
አባሪ አምስት፡- የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመና ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤት (ዋና ጥናት በሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) .............................................76

አባሪ ስድስት፡- ንኡሳን የመጻፍ ክሂሎች ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ............78
አባሪ ሰባት፡- የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ምስል............................................86
አባሪ ስምንት፡- በሁለቱ አራሚዎች የተሰጠ የፈተና ውጤት ናሙና.................................88
አባሪ ዘጠኝ፡- በቲ ቴስት ተሰልተው የተገኙ መረጃዎች....................................................89

## አህጽሮተ ጥናት (Abstract)

*ይህ ጥናት ዋነኛ አላማ አድርጎ የተነሳው ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱም ከፊል ፍትነታዊ ሲሆን የተካሄደውም በሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል የአስርኛ ክፍል ተማሪዎችን በዓላማ ተኮር የእጣ ንሞና ስልት ከተመረጡ በኋላ መደበኛ ትምህርቱን በአጥኚው የሚማሩ ሁለት ክፍል ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት ፈተናው ተሳትፈዋል፡፡ የሁለቱም ክፍል ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት ፈተናው ተቀራራቢ ውጤት በማስመዝገባቸው በተራ የእጣ ንሞና አንደኛውን ክፍል የሙከራ ቡድን ሌላኛውን ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ሆኖ በጥናቱ ውስጥ እንዲሳተፍ ተደርጓል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያነትም ለጥናቱ አስፈላጊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ፈተና ሆኖ በመገኘቱ በፈተና አማካኝነት መረጃው ተሰብስቧል፡፡ ፈተናው ቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተናን ያካተተ ነው፡፡ ቅድመ ትምህርት ፈተናው የተሰጠበት ዓላማ ተማሪዎች በተጠቀሱት ዘዴዎች ትምህርት ከመከታተላቸው በፊት ያላቸው የመጻፍ ክሂል ደረጃ ተቀራራቢ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተናው የተሰጠበት አላማ ደግሞ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ሆነው የተመረጡት ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማርያ ዘዴዎች የመጻፍ ክሂልን ከተማሩ በኋላ በመካከላቸው ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ነው፡፡ መተንተኛ ዘዴውን በተመለከተ ዳግም ልኬት ናሙና ቲ ቴስት (Paired sample T test) እና የሁለት ባዕድ ናሙናዎች ጥናት ቲ ቴስት (Independent Samples T test) የትንተና ዘዴዎች ተመርጠው በ “SPSS” የተሰላ ሲሆን በተገኘው ውጤት መሰረትም በቅድመ ትምህርት ፈተና ተቀራራቢ አማካይ ውጤቶች ያስመዘገቡ ቡድኖች በድህረ ትምህርት ፈተናው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ጉልህ የሆነ ልዩነት አሳይተዋል፡፡ (P= <0.05) ይህም ውጤት ሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ከማሻሻል አኳያ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ሊጠቁም ችሏል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ለተማሪዎች የሚቀርብበት መንገድ በመጻፍ ክሂላቸው ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ መፈተሽ ሲሆን እነዚህ የአቀራረብ መንገዶችም በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እድገት ላይ ወሳኝ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከመጻፍ ክሂል አቀራረብ መንገዶች ሂደታዊ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እድገት ላይ የሚኖረውን ሚና በተመለከተ ለጥናቱ መነሻ የሚሆኑ አበይት ጭብጦች እንዲሁም የጥናታዊ ስራውን ዘገባ አቀራረብ ስልት ጠቋሚ የሆኑ መሰረታዊ መረጃዎች ተጨምቀው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች የተካተቱትም በሚከተሉት የጥናትና ምርምር አላባዎች ውስጥ ነው፡፡ እነሱም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ መነሻ ችግር፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ መላምት፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣የጥናቱ ውስንነትና የቁልፍ ቃላት ብያኔ በምእራፍ አንድ ስር የተካተቱ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት ንድፈ-ሃሳባዊ እይታዎች፣ ፅንሰ-ሃሳባዊ እይታዎችና የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ተካተዋል፡፡ በምዕራፍ ሶስት ስር ጥናቱ እንዴት፣ በምን ዘዴ፣ እነማንን እንደሚያጠቃልል ገላጭ የሆኑ የጥናቱ ስነ-ዘዴ፣ የጥናቱ ንድፍ፣ የናሙና አመራረረጥ፣ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ፣ በምዕራፍ አራት የጥናቱ ትንተናና በምእራፍ አምስት የጥናቱ ውጤትና የመፍትሔ ሃሳብ ተገልጦበታል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ መፃፍ መሆኑ ይታወቃል፡፡ መጻፍ አንድን መልዕክት ለማስተላለፍ በትዕምርቶች (ምልክቶች) አማካኝነት ተቀርፆ የሚቀርብ ከመነሻው በንግግር የሚተላለፍን መልእክት ክፍተት በመሙላት አንድ ሃሳብ በቦታና በጊዜ ተጽእኖ ምክንያት ይፈጠር የነበረውን መዘንጋት መቅረፍ ያስቻለ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡

ይህን የመጻፍ ክሂል ለማስተማር በርካታ ተግባራትን መወጣት ይጠይቃል፡፡ በመጻፍ ክሂል ውስጥ የሃሳብ አደረጃጀት፣ የፊደላት አጣጣል፣ የቃላት አወቃቀር፣ የሐረጋት አመሰራረት፣ የዓረፍተነገር አደረጃጀት፣ በአንቀፅ ውስጥ የሀይለቃልና የዝርዝር ዓረፍተነገሮች አሰፋፈርና የሃሳብ አንድነት፣ ወዘተ ለመጻፍ ክሂል ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የመፃፍ ክሂል በኢ-መደበኛ ቀጥሎም በመደበኛ መንገድ መሰጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ሲተገበሩ ቆይተዋል፤ እየተተገበሩም ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ ውጤት ተኮር፣ ሂደት ተኮር፣ ሂደተ-ዘውጋዊ አቀራረብ ወዘተ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ውጤት-ተኮር አቀራረብ ሲሆን ቀደም ባሉት ጊዜያት በተለይም በ1960ዎቹ አካባቢ በስፋት ሲተገበር ቆይቷል (አማረ 2010)፡፡ የዚህ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ አላማ ተማሪዎች በቋንቋው ቅርፅ ላይ ተመስርተው የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማስቻል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከመዋቅራውያን አስተሳሰብ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ተማሪዎች ለቋንቋ ትክክለኛነት ትኩረት እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡

Kroll (1990) ገለፃ መሰረት ውጤት ተኮር አቀራረብ በተማሪዎች የእጅ ፅሁፍ ላይ ተመስርቶ የፅሁፉን የመጨረሻ ረቂቅ የሚገመግም፣ ዓረፍተነገርን በሚገባ በማዋቀርና በቋንቋው ህግ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ይህ አቀራረብ በተጠናቀቀ ፅሁፍ ላይ በማተኮር መፃፍን የሚያስተምር ጥንታዊ አቀራረብ ተደርጎ የሚቆጠር ከመሆኑም በላይ ተማሪው መምህሩ ከሚያቀርብለት ሞዴል ተመሳሳይ የሆነ ነገር እንዲፅፍ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪውን ፈጥሮ የመፃፍ ተነሳሽነት ይገድባል፡፡

መጻፍ በውጤት ላይ ያተኮረ ስለነበር መምህራን ተማሪዎች እንዲፅፉ መመሪያ ይሰጣሉ፤ በመጨረሻም ፅሁፉን ያርማሉ፡፡ እንጅ ተማሪዎች ደረጃ በደረጃ እንዴት መፃፍ እንዳለባቸው አያስተምሯቸውም፡፡ ስለሆነም እንዴት መፃፍ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ርዕስ መምረጥ፣ ማጥበብ (መወሰን) አስተዋፅኦ መንደፍ፣ መረጃ ማደራጀት የመጀመሪያ ረቂቅ መፃፍ፣ አርትኦት መስጠት፣ እንደገና መፃፍ የተሻለ ድርሰት እስኪጽፉ ድረስ ደጋግሞ መጻፍ የሚባሉ ሂደቶችን ለመተግበር ይቸገራሉ፡፡

በዚህ አቀራረብ መሰረት የትምህርቱ አላማ መሳካቱ የሚረጋገጠው በመጨረሻ በሚፅፉት ድርሰት ውጤታማነት ላይ በመመስረት ነው (Nunan 1989)፡፡ በመሆኑም የመምህራንን ሰፊ ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑ፤ የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚገድብ መሆኑ፤ በቋንቋው ቅርፅ ላይ የተመሰረተ መሆኑ፤ ለትክክለኛነት የሚጨነቅ መሆኑ … ክፍተቶችን የሚሞላ ሌላ የመጻፍ ክሂል የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ብቅ ሊል ችሏል (Kroll 1990)፡፡

ውጤት-ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በማዳበር በኩል ሰፊ ክፍተት ስለነበረበት ክፍተቱን ይሞላል ተብሎ የታሰበ ሌላ ሂደት-ተኮር አቀራረብ ብቅ ሊል ችሏል (Raimes 1983)፡፡ የሂደት ተኮር አቀራረብ ትኩረት ምን ተፃፈ ሳይሆን እንዴት ተፃፈ በሚለው የአፃፃፍ ሂደት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በመጨረሻ ላይ ከሚያቀርቡት ፅሁፍ ይልቅ በቅድመ-መጻፍ፣ በመጻፍ ጊዜና በድህረ- መጻፍ ላይ ያከናወኗቸው ተግባራት ላይ ልዩ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች ዋናውን ፅሁፍ ለማርቀቅ የሚያልፏቸው መንገዶች የተስተካከሉ ከሆኑ የተሻለ የመጻፍ ክሂል ሊያዳብሩ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ከውጤት-ተኮር አቀራረብ ሙሉ በሙሉ የተለየ አቀራረብ እንደሆነ (Yan 2005) ይጠቁማል፡፡

ሂደት-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ ለመፃፍ ደረጃ በደረጃ የሚያከናውኑት ተግባር፡- ሀሳብን ማፍለቅ እና ማደራጀት፣ በተደጋጋሚ ረቂቅ መፃፍ፣ ያረቀቁትን መከለስ፣ መሰረዝ፣ መጨመር፣ መቀነስ ደጋግሞ ሃሳብን ማደራጀት … ላይ የተመሰረተ ሲሆን በማረም ሂደቱም የቃላት መረጣ፣ የዓረፍተነገር አወቃቀርና የአፃፃፍ ስርአትን መከታተልና መረዳት ላይ የሚያተኩር ከመሆኑም ባሻገር ተማሪዎች የራሳቸውን ስትራቴጅ እንዲያዳብሩ የማስቻል ሚና አለው (አለምነሽ 2011)፡፡ በዚህም ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ቀዳሚ ተሳታፊ ናቸው፡፡ በመሆኑም በመፃፍ ትምህርት ካሉ አቀራረቦች ውጤታማ እንደሆነ ይገለፃል፡፡ ምክንያታቸውን ሲያቀርቡም ተማሪዎች ለመጻፍ ተግባራዊነት የራሳቸውን አካሄድ እንዲያዳብሩና በጥልቀት እንዲመረምሩ ስለሚያደርግ ነው (Richards 1990)፡፡

ሒደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ለመፃፍ የተመረጠውን ርዕስ በተመለከተ ሀሳብን በዝርዝር ማስፈር፣ ቢጋር (አስተዋጽኦ) መንደፍ፣ ረቂቅ መፃፍ፣ ረቂቁን ማስተካከልና ማሻሻል እንዲሁም የመጨረሻ ፅሁፍ መጻፍን ይይዛል (Byrne 1991)፡፡

የሂደት-ተኮር አቀራረብ ከሚቀርቡበት ትችቶች መካከል ተማሪዎች በራሳቸው ፍጥነት እየተለማመዱ የመጻፍ ስራቸውን ያከናውናሉ እንጅ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት እንዲያጤኑ የሚያደርግ አይደለም (Raimes 1983)፡፡ አቀራረቡ ምንም እንኳን መፃፍ ሂደታዊ ቢሆንም ተማሪዎች በመጨረሻ  በሚፅፉት ድርሰት ላይ ትኩረት አለመስጠቱ በድክመት የሚታይበት በመሆኑ ሌላ አቀራረብ ብቅ ሊል ችሏል፡፡

የሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ድክመቶችን ለማሻሻል ታስቦ የተጀመረው የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ሂደት-ዘውጋዊ (Process Genre) አቀራረብ ነው። ይህ አቀራረብ በተወሰነ መልኩ ከውጤት-ተኮር አቀራረብ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ይኸውም የመጻፍ ትምህርት ሲቀርብ ለሰዋስዋዊ ህግጋት ትኩረት ማድረግ አለበት ከሚል ሀሳብ መነሻነት የተፈጠረ ነው። አቀራረቡም የመጻፍ ትምህርት ሲቀርብ ከማህበረሰቡ አውድ ጋር በማጣጣም መሆን አለበት የሚል አስተሳሰብ ያራምዳል። በዚህም የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር የሚቀርቡ ይዘቶች የማህበረሰቡን ተግባቦት ባገናዘበ መልኩ ሰዋስዋዊ ህግጋትን ማስተማር አለበት የሚል አስተሳሰብ ያራምዳል (Hyland 2003):: ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን ይዘቶች መሰረት አድርገው ትርጉም እየፈጠሩ እንዲማሩ የሚያደርግ ቢሆንም ለተማሪዎች ፈጠራ የሚያነሳሳ አይደለም። እንዲሁም ከማህበረሰቡ ተግባቦት ጋር በተያያዘ መምህሩ ሰፊ ገለፃ የሚሰጥ በመሆኑ የዘውግ ተኮር  አቀራረብ ትችት ይደርስበታል (Nunan 1989)::

ሶስቱም አቀራረቦች የራሳቸው ድክመት የሚታይባቸው ቢሆንም የየራሳቸው ጠንካራ ጎኖች አሏቸው። ከሚነሱባቸው ትችቶች በመነሳት ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ከሁለቱ የተሻለ አቀራረብ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህም ከዚህ በፊት በተደረጉ የሀገር ውስጥና የውጭ ጥናቶች ላይ ተስተውሏል።

በሀገር ውስጥ ከተደረጉ ጥናቶች መካከል አለምነሽ (2011) በዚሁ ርዕሰ-ጉዳይ ዙሪያ ጥናት አካሂዳለች። በውጤቱም ሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በማዳበር አወንታዊ ተፅዕኖ እንዳለው አሳይታለች። ሌሎች መሰል ጥናቶችም ተዳሰዋል። ጥናቶችም ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ከተለመደው የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተሻለ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ማጎልበት እንደሚችል የሚያትቱ ቢሆኑም በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ፡- የይዘት፣ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የቃላት ምርጫ፣ የቋንቋ አጠቃቀምና ስርዐተ-አፃፃፍ ተተንትነው አልቀረቡም።

በመሆኑም በዚህ ጥናት አጥኚው ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር ያለውን ሚና ተንትኖ በማቅረቡ ከላይ ከተጠቀሱ ተዛማጅ ጥናቶች ልዩ ያደርገዋል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ቋንቋን የማስተማር ተቀዳሚ አላማዎች መካከል ተማሪዎች በዋና ዋና የቋንቋ ክሂሎች ተጠቅመው የተሻለ ተግባቦት እንዲፈጥሩ ማስቻል አንዱና ዋናው ነው፡፡ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል ማንበብና መፃፍ በትምህርት የሚገኙ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ መጻፍ ደግሞ ትዕምርቶችን በመጠቀም አንድን ሀሳብ (መልዕክት) ለሌሎች ለማስተላለፍ የምንጠቀምበት የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ ከዚህ ክሂል ጋር በተያያዘ በርካታ ጥናቶች ለረዥም ጊዜ ሲካሄዱ ቆይተዋል፤ እየተካሄዱም ይገኛሉ፡፡ መፃፍ የአፍልቆት ክሂል እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች ሀሳባቸውን፣ ስሜታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ወዘተ እንዲገልፁና ልዩ ልዩ ልምዶችን እንዲያከናውኑ የሚጠይቅ ክሂል ሲሆን ክሂሉን ለማሻሻል በርካታ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል (አማረ 2010)፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ተማሪዎች በክሂሉ ውስጥ ያሉትን አላባውያን ማለትም ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት፣ የቋንቋ አጠቃቀምና ስርዓተ-አፃፃፍን በተግባር መለማመድ ስላለባቸው ነው (Arininigsih 2010)፡፡

በመሆኑም ክሂሉ በትምህርትነት ሲሰጥ ከተማሪዎቹም ሆነ ከመምህሩ የሚጠበቁ ልዩ ልዩ ተግባራት አሉ፡፡ በተለይም ተማሪዎች ክሂሉን በተሻለ መልኩ ለማዳበር ሰፊ ልምምድና ብዙ ተግባራትን ማለትም፡- የሀሳብ አንድነት፣ ተለጣጣቂነት፣ ተከታታይነት፣ ከንግግር የተሻለ የቋንቋ አጠቃቀምን የቃላት መረጣ … ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም ሆነ በሌላ ምክንያት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን ሲማሩ የተለያዩ ችግሮች ይስተዋልባቸዋል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ትምህርት ሂደት ለሚፈጠሩ ችግሮች ከዚህ ቀደም አብዛኛዎቹ አጥኚዎች ከግል ገጠመኝ እንደሚነሱት ሁሉ አጥኚው ባስተማረባቸው ያለፉት ስምንት አመታት የተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ቀስ በቀስ እየወረደ ተማሪዎች መጠሪያ ስማቸውን መፃፍ እየተሳናቸው ሲመጣ በማስተዋሉ ለዚህ ድክመት ምክንያቱ የመጻፍ ትምህርት የሚቀርብበት መንገድ አንዱ ችግር መሆን አለመሆኑን ለማወቅ በመፈለጉና በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር በተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ላይ የሚኖረውን ሚና ለመፈተሸ ባደረበት ፅኑ ፍላጎት ይህን ጥናት ለማጥናት ተነሳስቷል፡፡

በመሆኑም ከመጻፍ ክሂል አቀራረቦች ውስጥ ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ ትኩረት በማድረግ በአዲዮ ወረዳ ከሚገኙ ሰባት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን በመውሰድ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች አላማ ተኮር ናሙናን

ተጠቅሞ በመምረጥ ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና ፈትሿል፡፡

ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የአስርኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂላቸውን ለማሻሻል ከተለምዷዊው የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በተለየ የሚኖረውን አስተዋፅኦ ፈትሿል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መላምት

ጥናቱ የሚከተሉትን አማራጭና አልቦ መላምቶችን አስቀምጧል፡፡

- የመፃፍ ክሂልን በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በተለምዷዊው የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተሻለ የመፃፍ ክሂል ችሎታ አላቸው፡፡
- የመጻፍ ክሂልን በሂደት ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተማሩ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በተለመደው መንገድ ከተማሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተሻለ የመጻፍ ክሂል ችሎታ የላቸውም፡፡

## 1.4 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ይህን አላማ ለማሳካት የሚከተሉትን ንዑስ ዓላማዎች አካቷል፡፡

- ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ ይዘትና የሀሳብ አደረጃጀት በማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና መፈተሽ!
- ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ የቃላት ምርጫና የቋንቋ አጠቃቀም ለማሻሻል ያለውን ሚና መፈተሽ
- ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ ስርዐተ-አፃፃፋቸውን ለማሻሻል ያለውን ሚና መፈተሽ

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ✓ ለመምህራንና ለተማሪዎች ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ፡- መምህራን የመጻፍ ክሂልን በሚያስተምሩበት ወቅት ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴን እንዲተገብሩ ያግዛል ተብሎ ይታሰባል፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማሳደግ ከመርዳቱ በተጨማሪ የመጻፍ ክሂል በሂደት የሚዳብር መሆኑን ተረድተው ሂደቱን ተከትለው የተሻለ ጽሁፍ እንዲጽፉ ያስችላቸዋል፡፡

1. እንዲሁም በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ተመሳሳይ ጥናቶች ለሚያደርጉ ምሁራን እንደመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሆኑት በ 2015 ዓ.ም በካፋ ዞን አዲዮ ወረዳ የሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በአዲዮ ወረዳ ከሚገኙ ሰባት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ያተኩራል፡፡

ጥናቱም ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና የሚፈትሽ ሲሆን በሌሎች ክሂሎች ላይ አላተኮረም፡፡

ከፅህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረቦችም ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና ብቻ ይፈትሻል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ መጻፍን በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሂደት-ተኮር ዘዴ ማስተማር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያሳየ ነው፡፡ በምርምር ስነ-ዘዴ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ አብዛኞቹ መጽሐፍት እንደሚገልጹት ይብዛም ይነስም ደረጃው ቢለያይም ማንኛውም ምርምራዊ ተግባር የራሱ የሆኑ ውስንቶች ሊኖሩበት እንደሚችል ይገመታል፡፡ እነዚህ ውስንነቶች በውስንነት ደረጃ የሚቀመጡት በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት ላይ ተጽዕኖ የማያሳድሩ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው፡፡

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመቀነስ የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ ቢሞከርም ከአቅም በላይ የሆኑ ነገር ግን በጥናቱ ውጤት ላይ ተጽእኖ የማያሳድሩ ውስንነቶች ተከስተዋል፡፡ ከውስንነቶች መካከልም በተለያዩ በአላት ምክንያት ለተወሰኑ

ሳምንታት ትምህርት በመቋረጡ አጥኚው በእቅዱ መሰረት ጥናቱን ለማካሄድ ከፍተኛ ችግር ገጥሞታል።

እንዲሁም በቁጥጥር ቡድኑም ሆነ በሙከራ ቡድኑ ለጥናቱ ተሳታፊ ይሆናሉ ተብለው በአጥኚው ከተመረጡት ተማሪዎች መካከል የተወሰኑ ተማሪዎች በትምህርት ቤት የማይገኙና በተከታታይ የሚቀሩ በመሆናቸው ከትምህርት ቤት አመራሮችና ከቤተሰብ ጋር በመነጋገር ተፈጥረው የነበሩ ችግሮችን በመቅረፍ ጥናቱ ላይ ተሳትፏቸው እንዲቀጥል ተደርጓል። እነዚህ ውስንነቶች በጥናቱ ውጤት ላይ የጎላ ተፅዕኖ ባለመፍጠራቸው በውስንነት ሊቀርቡ ችለዋል።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድሳናት

### 2.1 ከመጻፍ ጋር የተያያዙ የመማር ንድፈ-ሀሳቦች

የቋንቋ መማር ንድፈ-ሀሳቦች ላይ መሰረት ያደረጉ የጥናት ውጤቶችም ሆኑ ወደፊት ጥናት የሚደረግባቸው ንድፈ-ሀሳቦች በርካታ ቢሆኑም በዋናነት የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

#### 2.1.1 የጽሑፋዊ ንጽጽሮሽ ንድፈ-ሀሳብ (Contrastive Rhetoric Theory)

ይህ ንድፈ-ሀሳብ የተዋወቀው 1960ዎቹ በKaplan አማካኝነት ሲሆን ዋነኛ መነሻውም አፍ-ፈትና ኢ አፍ-ፈት ተናጋሪዎች መካከል የሚጻፉ ጽሁፎችን በማነጻጸር ነው፡፡ በ1960ዎቹ በአብዛኛው ይተገበር የነበረው የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ እዝነ ወልሳናዊ (አዳምጦ የመናገር ዘዴ) በመሆኑ ከማዳመጥና ከመናገር ውጭ ለሌሎች ክሂሎች ትኩረት የተነፈገበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት Kaplan የመጻፍ ክሂል ትኩረት እንደሚያስፈልገው በመረዳት በዚህ ንድፈ-ሀሳብ ላይ ሊመራመሩ ችለዋል፡፡ ጥናታቸውንም ለማካሄድ ከአውሮፓና ከእስያ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች እንደናሙና በመውሰድ ንጽጽራዊ ጥናቱን ለማካሄድ ችለዋል፡፡ የጥናታቸው ውጤትም በቻይንኛ፣ በአረብኛ፣ በአይሪሽ ፣በጃፓንኛና በፈረንሳይኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የጻፏቸው ድርሰቶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የተለዩ እንደሆኑ ለማሳየት ችለዋል፡፡

ይሁን እንጅ ይህ የንጽጽር ንድፈ-ሀሳብ ከትችት የጸዳ አልነበረም ቢሆንም የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት ውስጥ ንድፈ-ሃሳቡ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው ይነገራል፡፡ ይህን አስመልክቶ አማረ Silva (1990) በመጥቀስ እንደገለጹት የአንቀጽ አላባውያን የሚባሉት፡- ሀይለ-ቃል፣ ዝርዝር ዓረፍተነገሮችና መሸጋገሪያ ቃላት እንዲሁም ዛሬ ላይ በአንቀጽ ማስፋፊያ ውስጥ የሚጠቀሱትን የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎች የዚህ ንድፈ-ሀሳብ ውጤቶች እንደሆኑ ይጠቀሳል፡፡ ንድፈ-ሀሳቡ ለሰላሳ አመታት ተግባር ላይ ሲውል Conor (2002) ዋነኛ የንድፈ-ሀሳቡን የትኩረት አቅጣጫዎች በአራት ከፍለውታል፡፡

የመጀመሪያው የጽሁፋዊ ዲስኩር ትንተና ዘዴን በመጠቀም አንድ ጽሁፍ በተለያዩ ቋንቋዎችና ባህሎች እንዴት እንደሚተረጎም ማወዳደርና ማነጻጸር መቻል ነው፡፡ ሁለተኛው

የትኩረት ነጥብ የመጀመሪያ ቋንቋና ባህል በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ውስጥ ያለውን ተጽዕኖ መፈተሽ ነው። ሶስተኛው መማሪያ ክፍል ላይ የተመሰረተ ንጽጽሮሽ ሲሆን በመፃፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ ተማሪዎች የራሳቸውን ባህል ከሌላኛው ተማሪ ባህል ጋር እያነጻጸሩ የመደጋገፍ ተግባር በማሳየት የተሰጣቸውን ተግባር እንዲያከናውኑ መርዳት ነው። አራተኛው ዘውገ ውስን ፍተሻ ማካሄድ ነው። ይህም በስነ-ትምህርታዊ እና በአጠቃላይ የመጻፍ ሙያ ላይ የሚወሰን ነው።

የጽሑፋዊ ንጽጽሮሽ ንድፈ-ሀሳብ ለበርካታ አመታት ሲሰራበት ቢቆይም በዋነኝነት ሁለት መሰረታዊ ትችቶች ተነስተውበታል። የመጀመሪያው በመጻፍ ውጤት ላይ ብቻ ማተኮሩና ሂደቱን መዘንጋቱ ነው። ሌላኛው ትችት ደግሞ ንድፈ-ሀሳቡ ትኩረት ያደረገው በቴክስት (ገፀ-ጽሑፍ) ላይ እንጅ በአእምሯዊ ሂደታዊ ክንውኖች አለመሆኑ ነው (William & Kaplan 1996)። በዚህም የተነሳ ሌሎች ንድፈ-ሃሳቦች ተከትለው እንዲመጡ ምክንያት ሆኗል።

### 2.1.2 የግንዛቤ እድገት ንድፈ-ሀሳብ

ይህ ንድፈ-ሀሳብ ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው። ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ወይም አንቀፆች ላይ ግንዛቤ ተጽዕኖ እንዳለው ንድፈ-ሀሳቡ ይገልጻል። በእንግሊዝኛው የመፃፍ አውድ ውስጥ በመነሳት Flower and Hayes(1981) ያካሄዷቸው ጥናቶች የግንዛቤያዊ እድገት ንድፈ-ሀሳብ እንዲጠናከር ምክንያት ሆነዋል። በዚህ ጥናት መፃፍ፡- ማቀድን፣ ማፍለቅን፣ መተርጎምንና አርትኦት ማካሄድን የሚጠይቅ ተግባር እንደሆነ ተገልጧል። በዚህ ሞዴል መሰረት የመፃፍ ተግባርን ለማከናወን ተማሪዎቹ የሚያልፏቸው የመፃፍ ሂደቶች ተመሳሳይ ናቸው። ሆኖም ይህ ሞዴል በ Bereiter & Scardamalia (1987) ትችት ተንፀባርቆበታል። እንደነሱ አገላለጽ ሁሉም ጸሀፊዎች ተመሳሳይ ሂደት ሊያልፉ አይችሉም። በመሆኑም በ Flower & Hayes (1981) ሞዴል ጥሩና ደካማ ፀሀፊዎች የሚያልፏቸው ሂደቶች ለየብቻቸው ተነጣጥለው አልተቀመጡም በማለት ሞዴሉን ሊተቹ ችለዋል።

### 2.1.3 የተግባቦታዊ ንድፈ-ሀሳብ (Communication Theory)

ይህ ንድፈ-ሀሳብ በ1970ዎቹ አካባቢ ላይ የታየ ሲሆን ትኩረቱም በቋንቋ ተማሪዎች የተግባቦት ችሎታ ላይ ነው። በማንኛውም የመጻፍ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎቹ የሚያከናውኗቸው ተግባራት ተግባቦታዊ ሂደቶች ላይ የተመሰረቱ መሆን እንዳለባቸው ንድፈ-

ሀሳቡ ይገልፃል፡፡ በዚህ ንድፈ-ሀሳብ መሰረት በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ዲስኮርሶች የተለያዩ ተግባቦታዊ አላማ አሏቸው ብለው ያምናሉ፡፡ ይህንንም በተመለከተ አማረ (2010) Cooper & Odell (1977)ን በመጥቀስ እንደገለጹት የተለያዩ ጽሁፋዊ የዲስኩር አይነቶችን በዝርዝር ያስቀመጡ ሲሆን እነሱም ተውኔታዊ፣ ግለሰባዊ፣ ስነ-ትምህርታዊ ጽሁፎች፣ የንግድ ጽሁፎች፣ ቴክነኒካዊ ጽሁፎች፣ ልቦለዶችና ግጥሞች ናቸው፡፡ እነዚህ የጽሁፋዊ ዲስኩር መገለጫዎች ተግባቦታዊ አውዶች ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው በመጻፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ አወንታዊ ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህም ንድፈ-ሀሳብ ተግባቦታዊ ብልሀቶች የመጻፍ ትምህርቱን ለማሳለጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላላቸው ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አማረ (2010) Cohen (1998)ን በመጠቀስ ያስረዳሉ፡፡

#### 2.1.4 የማህበራዊ ግንባታውያን ንድፈ-ሀሳብ (Social Connstruction Theory)

ይህ Vigotsky (1978) ንድፈ-ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ሲሆን በዚህ ንድፈ-ሀሳብ መሰረት እውቀት ወይም ጽንሰ-ሀሳብ በቀላሉ የሚገኝ ወይም የሚፈጠር ሳይሆን ማህበራዊ አውዶች ላይ በመመስረት ሊገነባ የሚችል ነው አማረ (2010)፡፡ ይህ ንድፈ-ሀሳብ በመፃፍ ትምህርት አውድ ውስጥ የላቀ ድርሻ አለው፡፡ በዚህ ንድፈ-ሀሳብ ተመስርቶ የሚያስተምር መምህርም የጽህፈት ትምህርትን ማህበራዊና የዲስኩር አውዶችን በመቀላቀል ማስተማር አለበት፡፡

Zimmerman (1993) ገለጻ መሰረት ማህበረ-ግንባታውያን ንድፈ-ሀሳብ ተጠቅሞ የጽህፈት ክሂልን የሚያስተምር መምህር ትኩረቱ በሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ላይ ብቻ ሳይሆን ውጤት ተኮር ላይም ጭምር ነው፡፡ ተማሪዎች በጽህፈት ውጤቶች ላይ ተመስርተው የተረዱትን ትርጉም እየፈጠሩና እያደራጁ መሄዳቸው ውጤት-ተኮር አቀራረብ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ተማሪዎች ሃሳብ እየተለዋወጡ እየተደጋገፉ መስራት ማስቻሉ ደግሞ ሂደት-ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ላይ ያተኩራል አስብሎታል፡፡

በአጠቃላይ የማህበረ-ግንባታውያን አተያይ ተማሪዎች በአካባቢያቸው አውድ ላይ ተመስርተው እርስ በእርስ የሚፈጥሯቸው የሀሳብ መለዋወጦች የመጻፍ ክሂላቸውን ያሻሽላል የሚል አተያይ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

እንዲሁም Kroll (1990) Jonsan (1988)ን በመጥቀስ እንደገለጸው የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የሚያገለግሉ ሶስት ዋናዋና ንድፈ-ሀሳቦች አሉ፤ እነሱም፡- ሂደታዊ አቀራረብ (Process Approach)፣ ተራክቧዊ እይታ (Interactive View) እና የማህበራዊ እውቀት

ግንባታ (Social Contractivists) ናቸው፡፡ ሂደታዊ አቀራረብ በውስጡ ገለፃውያን (Expressivists) እና አእምሯውያን (Cognitivists) ያካትታል፡፡

በገለጻውያን ሀሳብ መሰረት መምህራን አዛዥ መሆን አይጠበቅባቸውም፡፡ ይልቁንም በክፍል ውስጥ የሚከናወነውን የመጻፍ ተግባር ጥሩ የሀሳብ ፍሰት ያለው ድርሰት እንዲጽፍ ለማድረግ ምቹ አጋጣሚ ይፈጥራሉ፡፡ የማስተማሪያ ፅሁፎቻቸውም ራስን መፈለግን የሚያበረታቱ የቤት ስራዎችን በመስራት ላይ እንዲያተኩሩ ያበረታታል፡፡ ይህም ተማሪዎች ነፃ ሆነው እንዲፅፉ ስለሚረዳ ሀሳባቸውን ለመግለፅ በርካታ ቃላት መጠቀም እንዲችሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ዋናው ነገር መፃፍ ግላዊ ድርጊት ሲሆን ጸሐፊው የሚጽፈው እውነታ ግን ከራሱ የመጣ ነው፡፡

በአእምሯውያን ንድፈ-ሀሳብ መሰረት መጻፍ የችግር መፍቻ ቁልፍ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ምክንያቱም መጻፍ የማሰብና የሂደት ውጤት ነው የሚል እምነት አለ፡፡ በጽሁፍ ውስጥ የሚካተቱ መረጃዎች በጸሀፊ አእምሮ ውስጥ የሚገኙ እንደሆኑ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በአብዛኛው እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎቻቸው ቅድመ-መጻፍ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ፡፡ በርካታ የጽሁፍ ረቂቆች እንዲዘጋጁ ያበረታታሉ፤ በየደረጃው ጽሁፋቸውን እንዲከልሱ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም ከመጨረሻው የአርትኦት ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ በዓረፍተነገር ደረጃ ያሉ ስህተቶቻቸውን እንዲያስተካክሉ ለተማሪዎች በመተው እነዚህን ተግባራት ሁሉ እንዲያከናውኑ ያዘጋጇቸዋል፡፡

ስለዚህ የመምህራን አላማ ተማሪዎች በመጻፍ ሂደት የሚሰሯቸውን ተግባራትና የሚያስፈልጓቸውን ቴክኒኮች የሚያውቁ ጥሩ ፀሀፊዎች እንዲሆኑ በማድረግ የፈጠራ ሂደታቸውን ይመራሉ በማለት Kroll (1990) ይገልፃሉ፡፡

በተራክቧውያን እይታ ደግሞ ፅሁፍ ፀሀፊው ከሌላ ሰው ጋር ምልልስ ለማድረግ የሚፈጥረው መግባቢያ በመሆኑ ፀሀፊውም ሆነ አንባቢው ለፅሁፍ ፍሰት ከፍተኛ ሀላፊነት መውሰድ እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

በማህበረ ግንባታውያን እይታ ደግሞ የጸሀፊው ሚና የሚገለጸው በማህበራዊ ስነ-ፅሁፍ ውስጥ ነው፡፡ የፅሁፍ ርዕሰ-ጉዳይ ውጤትም በአንድ ውስን አውድ እንደሚከናወን ማህበራዊ ድርጊት የሚቆጠር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት የመጻፍ ትምህርት ንድፈ-ሀሳቦች ውስጥ ይህ ጥናት የተከተለው የግንዛቤ እድገት ንድፈ-ሀሳብን ነው፡፡ ምክንያቱም ሂደት-ተኮር የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ከውጤት በበለጠ ለሂደቱ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ነው፡፡

## 2.2 የመፃፍ ክሂል ምንነት

መጻፍ ከአራቱ ዋናዋና የቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ የክሂሉን ምንነት አስመልክተው በርካታ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ሰንዝረዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል አማረ (2010) Raimes (1983) ጠቅሶ እንደገለጸው መጻፍ በጸሐፊና በአንባቢና መካከል የሚደረግ የተግባቦት ሂደት ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በጽሁፍ መልእክትን ማስተላለፍ ያለምንም አጋዥ በቀጥታ ለአንባቢው ማድረስ ላይ የሚያተኩር የመልእክት ማስተላለፊያ መንገድ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ በሌላ መልኩ Byrne (1988) አገላለጽ መሰረት መጻፍ ሆሄያትን በወረቀት ላይ ከማስፈር ከፍ ያለና በአእምሮ ያሰብነውን ሀሳብ ትዕምርቶችን በመጠቀም አስተሳሰብን ለአንባቢ አቀነባብሮ መልዕክት ማስተላለፍን ይመለከታል፡፡ Nunan (1989) በተመሳሳይ ጽህፈት አእምሮን ከሌሎች አካል ክፍሎች ጋር በማቀናጀት የሚከናወን የትዕምርቶች ውክልና ውጤት ነው በማለት የመጻፍን ምንነት ገልጸውታል፡፡

መጻፍ ማህበረሰብ በይሁንታ የተስማማባቸው ትዕምርቶች ማለትም ፊደላት ተቀርጸው እየተቀናጁ ለዚሁ ተግባር ተብለው በተዘጋጁ ወረቀት፣ ብራና፣ ማንኛውም ጠፍጣፋ ገጽታ ባለው ጽሁፍን በሚቀበል ነገር ላይ እንዲሁም ቴክኖለሎጅን በመጠቀም ሀሳብን አደራጅቶ የማስፈር ሂደት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የምንጽፋቸው ዓረፍተነገሮች እርስ በርሳቸው የሀሳብ ቁርኝት ያላቸው ተጠየቃዊ የሆነ፣ ፍሰታቸውን የጠበቁ፣ ተለጣጣቂነትና ወጥነት ያላቸው፣ የቋንቋውን ስርዓት የጠበቁ፣ ጥምረት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ደግሞ ግዴታ ነው፡፡ የመጻፍ ክሂል እንደማናቸውም የተቀሩት የቋንቋ ክሂሎች የራሱ የሆነ የተለየ ባህሪ አለው፡፡ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ሁለቱ ማለትም ማንበብና ማዳመጥ የሌሎችን ስሜት የመቀበልና የመረዳት ሁኔታዎችን ስለሚያሳዩ የመረዳት ክሂሎች ሲባሉ መናገርና መጻፍ ደግሞ ተናጋሪው ወይም ጸሀፊው የራሱን ስሜት ለሌሎች የማንጸባረቅ ሁኔታን የሚያመለክትባቸው በመሆናቸው የገለጻ ክሂሎች ሊባሉ ይችላሉ፡፡

መጻፍ የንግግር ወኪል ነው፡፡ ቦታና ጊዜ በለያያቸው ሰዎች መካከል በምልክቶች አማካኝነት ግንኙነት ለመፍጠር ራስን ለመግለጽ እንዲሁም መረጃ መለዋወጥ በቋንቋ መጠቀም ማለት

ነው፡፡ መጻፍ ሀሳብን ቋሚና እይታዊ በሆኑ ትእምርቶች ቀርጾ ለማቆየት የሚያስችል በቦታና በጊዜ የማይወሰን ህያው ነው፡፡ ስለሆነም መጻፍ ሀሳብን ምልክትን በመጠቀም ለሚፈለገው አላማ መጠቀም ማለት ነው፡፡

መጻፍ መጠነ-ሰፊ የሆነ የሀሳብ አሰሳ የሚካሄድበት ከመሰረታዊ ክሂሎች አንዱ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በማጠናከር በድሉ (1996) እንደገለጹት መጻፍ ጥልቅ የሆነ የመረጃ መሰብሰብ የሚታይበት ሂደት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ይህ የሚያመለክተው ስሜታችን በወረቀት ከማስፈራችን በፊት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሀሳብ ማከማቸትና መለየት የሚጠይቅ ክሂል ነው፡፡

ደሳለኝ (1994) ሲገልጹ የመጻፍ ክሂል ይዘት ባጭሩ ከእጅ ጽህፈት ሆሄያት አጣጣል ጀምሮ ሀሳብን በተገቢ መንገድ ወረቀት ላይ እስከማስፈር ያለውን ሒደት የሚያጠቃልል ሰፊ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ ሀሳብን በወረቀት ማስፈር ሲባል የውስጥ ስሜት ያፈለቃቸው የተለያዩ ቁምነገሮች ወይም መልዕክቶች አንባቢ ወይም ተቀባይ ሊገነዘበው በሚችለው አግባብ የተመረጡ ቃላትን በመጠቀም ማራኪ የሆነ የዓረፍተነገሮችንና የአንቀጽ አደረጃጀትን በመከተል ድርሰቶችን መመስረትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

ከላይ ከቀረቡ ትንታኔዎች የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመጀመሪያ መጻፍ ጸሀፊው ከእለት ተዕለት ገጠመኞች ላይ ተመስርቶ ከአንባቢው ጋር ለመግባባት የሚጥርበት ክሂል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መጻፍ አእምሯዊ ተግባር እንደሆነና የተለያዩ ትዕምርቶችን በመጠቀም አስተሳሰብን፣ ስሜት፣ ፍላጎትን የመግለጽ ሂደት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተጨማሪም ማረው (1996) የመጻፍ ምንነትን ሲገልጹ መጻፍ ክሂለ-ብዙ ተግባር ነው፡፡ ርዕስ የመምረጥና የማጥበብ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የዓረፍተነገር አወቃቀር፣ የሀሳብ አፈላለቅና አደረጃጀት፣ የአንቀጽ አደረጃጀት ብሎም ሙሉ ድርሰት የመጻፍ ችሎታዎችን ይጠይቃል፡፡ ክሂሉ እየጻፉ መማርን የሚጠይቅ በመሆኑ ወደጽሁፉ ስራ ከመገባቱ በፊት እና በኋላ በርካታ ሂደቶችን ማለፍ የግድ ይላል፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው መጻፍ ውስብስብና በርካታ ተግባራትን ማከናወን የሚጠይቅ ክሂል መሆኑን ነው፡፡ እነዚህም ከርዕስ መረጣ እስከ ድርሰት መጻፍ እንዲሁም ከፊደላት አጣጣል ሀሳብን በተገቢው መንገድ አደራጅቶ እስከማስፈር የሚከናወን ተግባር መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

እንዲሁም መጻፍ በቋንቋ ትምህርት ላይ ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ በርካታ ምሁራን ሀሳባቸውን ሲገልጹ ተስተውሏል፡፡ ከነዚህም መካከል አማረ (2010) Mercer (1989)ን በመጥቀስ እንደገለጹት የመጻፍ ትምህርት በዋነኝነት ሶስት መሰረታዊ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎች ስለመጻፍ ምንነት ተረድተው የተለያዩ ተግባራትን በክፍል ውስጥ ያከናውናሉ፡፡ እንዲሁም መጻፍ ለሌሎች የትምህርት አይነቶችም የራሱን ሚና እንዲወጡ ያግዛል፡፡ በክፍል ውስጥ ያከናወኗቸው የመጻፍ ተግባራት ከክፍል ውጭም የተለያዩ ተግባራትን እንዲወጡ ያስችላል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ከፍ ያሉ የመጻፍ ስራዎችን ከመፃፍ ባሻገር የማንበብ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

White & Hardint (1991) የመጻፍን ምንነት ሲገልጹ ንግግርን በምልክት ከማስፈር በላይ የሆነ ራሱን የቻለ የማሰብ ሂደት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

Zamel (1982) በበኩላቸው መጻፍ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች የሚፈረጅ ሂደታዊ የሆነ፤ ዓላማ ያለው፤ አሳታፊ፤ አሳሽና ተመላላሽ ሂደትን የሚከተል እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ መጻፍ ተግባቦታዊ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የጸሀፊውና የአንባቢው ግንኙነት፣ መልእክቱ የሚተላለፍበት መንገድ፣ የቃላት መረጣ፣ የሀሳብ አደረጃጀት የሚሉትን ሁሉ ያካትታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የመጻፍ ትምህርት ከፊደላት አጣጣል ጀምሮ እስከ ድርሰት መጻፍ የሚደርስ ተግባራት የሚከናወኑበት ክሂል በመሆኑ ለቃላት አጠቃቀም፣ ለአጻጻፍ ስልት፣ ለሀሳብ አደረጃጀት፣ ለሰዋሰው ስርዓት... እውቀትን የሚጠይቅና መተግበርን የሚፈልግ ክሂል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የመጻፍ ትምህርት በክፍል ውስጥ የሚከናወን ይሁን እንጅ ተግባራቱ በክፍል ውስጥ ብቻ ተገድበው የሚቀሩ አለመሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.3 የመጻፍ ትምህርት ዓላማ

መጻፍ በትምህርትነት የሚሰጥበት የተለያዩ ዓላማዎች እንዳሉት ከሚገልጹ ምሁራን የተወሰኑትን ሀሳብ በዚህ ጥናት ላይ ለማካተት ተሞክሯል፡፡ ከነዚህ መካከል Raimes (1983) ገለጻ ተማሪዎች መጻፍን የሚማሩባቸው ዓላማዎች ዓረፍተነገርን ከመጻፍ በዘለለ መልኩ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም ጸሀፊው ከአንባቢው ጋር ለሚፈጥረው ተግባቦት፣ እውቀትን ለመገብየት፣ የዕለት ተዕለት የህይወት ገጠመኞቹን መዝግቦ ለማስቀመጥ

እንዲሁም ታሪክን ለትውልድ ከማስተላለፍ በተጨማሪ በንግግር የሚተላለፍ መልዕክት የሚታይበትን የጊዜና የቦታ ውስንነት ለመቅረፍ ሲባል የመጻፍ ትምህርት ይሰጣል። ምሁራኑም የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት ውስጥ ሊተኮርባቸው ከሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል ርዕቱነትና ትክክለኛነትን ይጠቅሳሉ። ርዕቱነት በሂደት ሊዳብር የሚችል የመጻፍ ትምህርት አንዱ አቅጣጫ ሲሆን ትክክለኛነት ደግሞ በታላሚው ቋንቋ መዋቅር ላይ ትኩረት ያደረገ የትምህርት ሌላኛው አቅጣጫ ነው። በመሆኑም መዋቅር ላይ ማተኮሩ ትክክለኛነት ሲሆን ተግባቦቱ ደግሞ ርዕቱነትን ያሳያል። እንዲሁም የመጻፍ ትምህርት ዓላማን ከንዑሳን ክሂል አላማዎች ጋር በማያያዝ ሀሳባቸውን ይገልጻሉ። ይኸውም የመጻፍ ክሂልን መማር የተለያዩ የመጻፍ ንዑሳን ክሂሎችን የመለየት ተግባር ይጠይቃል።

መጻፍ እንደመናገር በቀላሉ የምንለምደውና የምንማረው ሳይሆን በስርዓት መማርንና ማሰላሰልን የሚጠይቅ ውስብስብ ክሂል ነው። ይሁን እንጅ ብዙዎቹ ለክሂሉ የሚሰጡት ዋጋና ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ የመጻፍ ክሂል የሚፈለገውን ያህል አልጎለበተም። ይህን መሰሉን ችግር በመቅረፍ የተማሪዎች ችሎታ እንዲጎለብትና ትምህርትን ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲካሄድ ለማድረግ ማስተማር አስፈላጊ ነው።

በተጨማሪም እንደ Gerant (1987) ገለጻ ተማሪዎች መጻፍን የሚማሩበት ዋናው ዓላማ ለሚቀርብላቸው ማንኛውም አይነት ጥያቄ ተገቢና ትክክለኛ መልስ በጽሁፍ መስጠት እንዲችሉና የመጻፍ እውቀትን ለማሳደግ አጋዥ በመሆኑ ነው። የመጻፍ ክሂል ለመግባቢያነት ከማገልገል ባለፈ ሌሎችን ትምህርቶች ለመማር ስለራሳችንና ስለሌሎች ለማወቅ፣ የረቀቀ አስተሳሰብን ለማጎልበት፣ ከአለም ህዝብ ጋር መረጃ ለመለዋወጥ እንደሚረዳ Miller (1999) ገልጸዋል።

የመጻፍ ክሂል በመርሀ-ትምህር ላይ የሰፈረና እንደ መግባቢያነት ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን የተማሪዎችን የሰዋሰው አወቃቀርና የቃላት እውቀት ለማጎልበት እንዲሁም አዳዲስ ቋንቋና ከተለያዩ ዘዴዎች ጋር ለመተዋወቅ እድል ይፈጥራል። የመጻፍ ክሂል ከትምህርት አንጻር ሲታይ የሚከተሉት ዓላማዎች እንዳሉት Byrne (1991) ይገልጻሉ። እነሱም፡-

- ✓ ከተለያዩ የጽሁፍ ቅርጾች ጋር መተዋወቅና ልምምድ ማድረግ የተለያየ የመማር ስልትና ፍላጎትን ለመለየት ያስችላል።
- ✓ በተማሪዎች ላይ ስለተፈጠረው ለውጥ ተጨባጭ መረጃ ይሰጣል።

- ✓ መጻፍ እንደ አንድ ማስተማሪያ ዘዴ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡
- ✓ ተማሪዎች የክፍል ተግባራትን በግልና በቡድን እንዲተገብሩ ከማስቻሉም በላይ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን የማሰቢያ ጊዜ እንዲያገኙ ያስችላል፡፡
- ✓ መደበኛም ሆኑ ኢ መደበኛ ፈተተናዎችን ለማቅረብ ያስችላል፡፡

Wigand (1986) ተማሪው መጻፍ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በሚጽፍበት ጊዜ የመጻፍ ተግባቦትን አላማ ለይቶ በማወቅ ክሂሉን በአግባቡ መጠቀም እንዲችል በቂ የመጻፍ ትምህርት ያስፈልገዋል፡፡ በትምህርቱም ወቅት ለምን፣ ለማንና እንዴት እንደሚጽፍ በመጠየቅ እንደሚጽፍበት ዓላማ የመጻፍ ክሂሉን የሚያዳብረው መጻፍን ሲማር ነው በማለት መጻፍ የማስተማር አስፈላጊነትን ይገልጻሉ፡፡

Celce Murcia (1991) ገለጻ መሰረት ተማሪዎች የፊደልን ቅርጽ በመለየት ቃላትን መስርተው የቃላትን ምርጫና አጠቃቀም በማወቅ ሀሳባቸውን በተገቢ ቃላትና ዓረፍተነገሮች ማስተላለፍ የሚችሉበትን የተግባቦት ስርዓት እንዲያውቁ መጻፍን ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እነንደሚቻለው በትምህርት ቤት መጻፍ የሚማሩ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ፊደል ከመለየት ጀምረው ሀሳባቸውን በብቃት መግለጽ እስከሚያስችላቸው ሰፊ የጽሁፍ መዋቅር ድረስ እንደሚያስፈልጋቸው ነው፡፡

የመጻፍ አስፈላጊነት ሰዎችን ከማግባባቱ ወይም የቦታና የጊዜ ውስንነትን ከመፍታት አልፎ አገልግሎት መስጠት ከመቻሉ አኳያ ብቻ የሚታይ አይደለም (Raimes 1983)፡፡ መጻፍ ከተግባቦት መሳሪያነቱ ባሻገር የተለያዩ እውቀቶችን መቅሰሚያ፣ የሀሳብ ማሰባሰቢያና ማሳያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ስለዚህም መጻፍን መማር ተማሪዎች የፈርጀ-ብዙ አገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ Byrne (1991) የመጻፍን ትምህርት አስፈላጊነት ከስነትምህርታዊ ጠቀሜታው አኳያ የገለጹት የጽሁፍን ፈተናን ለመስራት፣ ሌሎች ክሂሎችን ለመማርና በንባብ የሚከናወኑ የመማሪያ አውዶችን ለመፍጠር ያስችላል በማለት ነው፡፡

የመጻፍ ትምህርት አስፈላጊነት ከግለሰባዊና ከማህበረሰባዊ ጠቀሜታ አንጻር ማየት ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት መጻፍን መማር ለግለሰቡ አመለካከቱን ለመግለጽና ለማሳወቅ አእምሯዊ ተግባረራትን ለማከናወንና የተጻፉ ሰነዶችን ለመመርመር ለማህበረሰቡም የጽሁፍ ቋንቋን

ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ የስነ-ጽሁፍ ስራዎችንና ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለማጠራቀም የሚያገለግል መሆኑን (Bradley 1994) ይገልጻሉ፡፡

Heaton (1991) በበኩላቸው መጻፍን ማስተማር በመደበኛ ትምህርት የሚዳብሩትን የጽሁፍ ተግባቦት ለማካሄድ፣ ሀሳብንና ስሜትን ለመግለጽ የሚያስችሉትን የመጻፍ ክሂሎችን ማዳበር መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም መጻፍን ማስተማር የሚከተሉትን ችሎታዎች ለማዳበር እንደሚያገለግል ይገልጻሉ፡፡ እነሱም፡-

1. ማስተላለፍ ለሚፈለገው ሀሳብ ተገቢ የሆኑ የአጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ፣ የዓረፍተነገር አመሰራረትና የአንቀጽን አወቃቀር ስርዓት ጠብቆ የመጻፍ፣ የተለመደና መደበኛ ቋንቋን የመጠቀም ብቃትን ያዳብራል፡፡
2. ሰዋስዋዊ ክሂሎችን በመማር ተገቢ የሆኑ ዓረፍተነገሮችን መስርቶ የመጻፍ ብቃትን ያጎለብታል፡፡
3. ግላዊ ስሜትን ለመግለጽ የሚያስችሉ ቃላትንና ዓረፍተነገሮችን የማፍለቅ ችሎታን ያዳብራል፡፡
4. ተገቢ የሆኑ ቃላትን በመምረጥ ዓላማን ወስኖ ለአንባቢ የማቅረብ ብቃትንና የሀሳብ አደረጃጀትን ትክክለኛነት ጠብቆ መረጃዎችን በቅደምተከተል አቀናብሮ የመግለጽ ችሎታን ያዳብራል፡፡
5. የጽሁፍ ቋንቋ መግለጫ የሆኑትን የስርዓተ-አጻጻፍ ደንቦችን ተገንዝቦ በተገቢው መንገድ በአገልግሎት ላይ የማዋል ብቃትን ያስገኛል፡፡
6. ለማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ተገቢና ተስማሚ የሆኑ ቃላትን መርጦ ማስተላለፍ፣ የሀሳብ አቀራረብን ሚዛናዊነት ጠብቆ ክስተቶችን ወይም ድርጊቶችን በቅደምተከተል አቀነባብሮ የመግለጽችሎታ ማዳበር የሚሉት ናቸው፡፡

Byrne (1991) የመጻፍ ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ በጽሁፍ የተደገፈ ትምህርት በተማሪዎች ዘንድ የተነሳሽነትና በራስ የመተማመን ስሜትን ያጎለብታል፡፡ ተማሪዎችም በየትምህርት አይነቱ መሻሻል ማሳየታቸውን ያረጋግጣል በማለት ገልጸውታል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ ከተነሱ ሀሳቦች የመጻፍ ክሂልን ማስተማር ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ህግጋትን በአግባቡ ተጠቅመው ሀሳባቸውን በጽሁፍ አማካኝነት እንዲገልጹ ለማስቻል በቋንቋው በሳል የአጠቃቀም ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ተገቢ የሆኑ የቃላት አወቃቀሮችንና የቋንቋ

አጠቃቀሞችን በጥቅም ላይ በማዋል በእነሱና በአንባቢያቸው መካከል ጤናማ የሆነ መግባባትን ለመፍጠርና በመጻፍ ክሂል ትምህርት ልምምድ ወቅት ሌሎች ክሂሎችንም ጭምር እንዲያዳብሩ ለማድረግ እንደሚያግዝ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.4 በመጻፍ ትምህርት ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮች

ምሁራን መጻፍ ብዙ ጥረትን የሚጠይቅ አእምሯዊ ተግባር እንደሆነ ይስማማሉ፡፡ አእምሯዊ ጥረትን የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑም ተማሪዎች አንድ ጽሁፍ ለመጻፍ በሚሞክሩበት ሰዓት በርካታ ችግሮች ይገጥሟቸዋል፡፡ Byrne (1988) ገለጻ መሰረት መጻፍ ከሌሎች ክሂሎች በተለየ መልኩ አስቸጋሪ የሚያደርጉት ነጥቦችን በሶስት ከፍለው አስቀምጠዋቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ስነ-ልቦናዊ ችግር ነው፡፡ለምሳሌ፡- አንድ ጸሀፊ በሚጽፍበት ጊዜ ከአንባቢ የሚያገኘው ቅጽበታዊ ምላሽ ባለመኖሩ ይጨነቃል፡፡ ሌላው ስነ-ልሳናዊ ችግር ሲሆን መጻፍ ከንግግር በበለጠ ለሰዋሰውም ሆነ ለተግባቦት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ለትክክለኛነት ይጨነቃል፡፡ ሌላው ግንዛቤያዊ ችግር ነው፡፡ በንግግር የሚገለጽ መልዕክት የመጻፍን ያክል ግንዛቤን ላይጠይቅ ይችላል፡፡ አማረ ((2010) Mohamed (2007)ን በመጥቀስ እንደገለጸው ተማሪዎች በመጻፍ ትምህርት ሂደት ከፊደል አጻጻፍ፣ ከስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም፣ ከይዘት፣ ከቃላት አመራረጥ፣ ከዓረፍተነገር አወቃቀር፣ ከአንቀጽአደረጃጀት … አንጻር የሚከሰቱባቸው ችግሮች አሉ፡፡

በአጠቃላይ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ሂደት በተማሪዎች ላይ የስነነ-ልሳናዊ፣ የስነ-ልቦናና የግንዛቤ ችግሮች ከመከሰታቸውም በተጨማሪ ከፊደላት አጣጣል ጀምሮ በሚከናወኑ ሂደቶች ላይ ችግሮች ይገጥሟቸዋል፡፡

## 2.5 መጻፍን ማስተማሪያ መርሆዎች

እንደሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ሁሉ የመጻፍ ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን ማስተማሪያ መርሆዎችንና ቅደምተከተሎችን መሰረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ Ur (1996) ይህን ሀሳብ በማጠናከር የመጻፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት መምህራን ክሂሉን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ክንዋኔዎችን በጥንቃቄ ሊመርጡ እነንደሚገባና ሲመርጡም የሚከተሉትን የመጻፍ ክሂል መልመጃ ክንዋኔዎች በመጠቀም ሊሆን እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

መልመጃዎቹ ተማሪዎችን ማበረታታት፣ ማነቃቃትና መሳብ የሚችሉ ናቸውን? ደረጃቸውንስ የሚመጥን ነው? ፍላጎታቸውንስ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው? መልመጃዎቹን ከመስራታቸው በፊት ፍንጭ ያስፈልጋቸው ይሆን? በአጠቃላይ ተግባራቱን የሚወዷቸውና ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ መጻፍን ለማስተማር ልንከተላቸው የሚገቡ አጠቃላይ መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ የመጻፍ ክሂል በክፍ ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ሊከናወን ይችላል፡፡ ይሁን እንጅ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው ትምህርት ጊዜውን በሰዋሰውና በቃላት ላይ ብቻ የሚያጠፋ መሆን የለበትም፡፡
- ✓ የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እንዲዳበብር ከተፈለገ የመጻፍ ክሂልን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ተግባራት በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ መስራት ይገባል፡፡
- ✓ የመጻፍ ተግባራት በሚታቀድበት ጊዜ ፍላጎትና ተነሳሽነትን የሚፈጥር፣ አላማ ያለው፣ አውድን መሰረት ያደረገ፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ደረጃና ዳራዊ እውቀት ያገናዘበ፣ ተማሪዎች ንድፍ እንዲያዘጋጁና በሂደት ንድፉን እንዲያሻሽሉ የሚያበረታታ፣ መጻፍን ከሌሎች ክሂሎች ጋር አጣምሮ የሚያቀርብ መሆኑን ማገናዘብ ያሻል፡፡
- ✓ ተማሪዎች እንዲጽፉ ከመደረጉ አስቀድሞ እንዲዘጋጁ እድል የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ✓ የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት፣ የተማሪዎችን በራስ መተማመንና ችሎታ የሚያዳብር ክንዋኔዎችን ማካተት ይኖርበታል Ur (1996)::

በተመሳሳይ Hilloks (1986) ጥሩ የጽሁፍ ማስተማሪያ ዘዴ የሚከተሉትን ባህሪያት ማሟላት እንዳለበት ሲያስረዱ፡- ረቂቅ መጻፍ፣ አቀናጅቶ መጻፍና መከለስን ሊይዝ ይገባል፡፡ ግልጽና የታወቀ አላማ መኖር አለበት ተጨባጭ መረጃን በመጠቀም እገዛ ማድረግና ምጋቤ ምላሽ መስጠትን የሚያካትት ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Byrne (1991) በበኩላቸው መጻፍን በምናስተምር ጊዜ ተማሪዎች በቂ ልምምድ እንዲያደርጉ መርዳት፣ የጽሁፋዊ ቋንቋን ተገቢነት በተጨባጭ ማሳየት፣ ተአማኒነት ያላቸውና የተማሪዎችን ፍላጎት የሚስቡ ክንዋኔዎችን ማዘጋጀት፣ መጻፍን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማስተማር፣

ለተማሪዎች ተገቢውን እገዛ ማድረግና ሀሳባቸውን መካፈል የማስተማሪያ ዘዴን ስኬታማ ለማድረግ አጋዥ መሆኑን አስረድተዋል።

## 2.6 የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች

### 2.6.1 ውጤት-ተኮር አቀራረብ (Product approach)

ውጤት-ተኮር አቀራረብ ከረዥም ጊዜ አንስቶ መጻፍን በማስተማር ሂደት ሲያገለግል የቆየና በአሁኑ ጊዜም ለተለያዩ አላማዎች በማገልገል ላይ ያለ የመጻፍ ትምህርት ማቅረቢያ ስልት ነው። ይህ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ የመጨረሻ ውጤትና በቋንቋው ቅርጽ ላይ ነው(Richards 1990):: ይኸውም ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ጽሁፎች ምሳሌ ይሆናሉ ወይም ጥሩ ተጽፈዋል ተብለው የሚታሰቡ ጽሁፎችን በሞዴልነት አቅርቦ ሰዋስዋዊ ህጎችን፣ አደረጃጀትን፣ የአጻጻፍ ብልሀትን … በማሳየት ተማሪዎች እነዚያኑ አስመስለው እንዲጽፉ የሚያለማምድ ነው (Nunan 1989):: በዚህዘዴ ዓላማ መሰረት ተማሪዎች የሚጽፉት የሰዋስው፣ የፊደል አጣጣልና ሌሎች ስህተቶችን ለማስተካከል ሲሆን በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው የመጻፍ ተግባራት በቋንቋው ሰዋስው ላይ ያተኮሩ ናቸው። ተማሪዎቹ በሞዴልነት በቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ጾታን፣ ጊዜን፣ ቁጥርን ወዘተ. በመቀየር የሚለማመዱባቸው ጠቋሚ መልመጃዎች ይቀርባሉ። በመምህሩ ተመርጦ በሚሰጣቸው ርዕስ ድርሰት ሲጽፉ መጀመሪያ ትኩረታቸውን በቋንቋው መዋቅር ላይ እንዲያደርጉ ይጠበቃል። ሰዋስዋዊ ስህተቶችንም ለማስወገድ ሲሉ በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይደረጋል (Leki 1996)::

በከፍተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የዚህ አቀራረብ ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው በተለያዩ አንቀጾችና አውዶች መዋቅርና አደረጃጀት ላይ ነው። ዓላማውም ትክክለኛ ጽሁፎችን ማፍለቅ ነው። ዋናዋና ባህርያቱና መርሆዎቹ የመሚከተሉት እንደሆኑ Richards (1990) ይገልጻሉ።

1. የድርሰት አጻጻፍ መመሪያዎችንና የሰዋስው ህጎችን በተለያዩ የድርሰት አይነቶች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በማሳየት ተማሪዎቹ በተግባር እንዲለማመዷቸው ያደርጋል።
2. የመጻፉ ዓላማ ተማሪዎች በትምህርት ተቋም ወይም በግል የሚተገብሯቸውን ጽሁፎች መጻፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው። በተለያዩ የድርሰት አይነቶች ቅርጽና አደረጃጀት ላይ ያተኩራል።

3. ትክክለኛ የዓረፍተነገር መዋቅር መስራት የትምህርቱ አስፈላጊ አካል ነው፡፡ ስለዚህም የሰዋስው ችሎታ ከፍተናውን ቦታ ይይዛል፡፡
4. ሞዴሎችን በማቅረብ ተማሪዎች አስመስለው እንዲጽፉና ስህተት እንዳይሰሩ ለማድረግ ይሞከክራል፡፡
5. የእጅ ጽሁፍ፣ የስርዓተነጥብ፣ የቃላት አገባብ፣ የፊደል አጣጣል፣ ወዘተ እውቀቶች በትምህርትነት ይሰጣሉ፡፡

በውጤት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ትምህርቱ የሚቀርብበት ቅደምተከተል የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን በተናጠል ከመመስረት ጀምሮ አንቀጾችን መገንባት ቀጥሎም የተለያዩ ድርሰቶችን ወደ መጻፍ የሚሄድ ነው፡፡ በዚህም ሰዋስዋዊ ህግጋት፣ የአንቀጽ አገባብ እውቀትና የድርሰት አይነቶች በትምህርትነት ይሰጣሉ፡፡ ልምምዶችም ሞዴሎችንና የዓረፍተነገር አመሰራረት ሰዋስዋዊ ህግጋትን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

**2.6.1.1 የውጤት-ተኮር አቀራረብ የመጻፍ ደረጃዎች**

በውጤታዊ አቀራረብ መጻፍን በማስተማር ሂደት በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ እነዚህም ተግባራት፡- ውስን መጻፍ፣ ምር መጻፍና ነጻ መጻፍ ደረጃዎች ናቸው (Richards 1990)::

**ሀ.ውስን መጻፍ (controlled writing)፡-** ለመጀመሪያ ደረጃ የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ለሚካሄድ የመጻፍ ትምህርት የሚቀርብና የውስንነት ደረጃው ፍጹም ወይም አንጻራዊ የሆነ ክንውን ነው፡፡ የዚህ የመጻፍ ስራ ዋና ዓላማ ተማሪዎች አንጻራዊ በሆነ መንገድ ከስህተት የጸዳ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ ነው፡፡ በውስን የመጻፍ ደረጃ መጻፍን ለማስተማር የሚቀርቡት ይዘቶች ውስን ማሰብንና ማፍለቅን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በውስን የመጻፍ ደረጃ ባዶ ቦታዎችን መሙላት፣ በሰንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን በማቀናጀት ዐረፍተነገር መስራት፣ ቅደምተከተላቸው የተፋለሱ ቃላትን በማስተካከል ዐረፍተነገር መስራት በአንቀጽ ውስጥ የቁጥር፣ የጾታ፣ የጊዜ፣ ወዘተ ለውጥ በማድረግ እንደገና መጻፍ የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል (Kroll 1991):: በዚህ ዘዴ የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎች ወደ ብዙ ስህተት እንዳያመሩ ቁጥጥር የሚያደርጉ ሲሆን አብዛኛው ትኩረታቸው በሰዋስው አገባብና አጻጻፍ ዘዴ ላይ በመሆኑም ከርቱዕነት ይልቅ ለትክክለኛ ቋንቋ አጠቃቀም ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡

**ለ. ምር መጻፍ (Guided writing)፡-** ምር መጻፍ በውስንና በልቅ መጻፍ መካከል እንደድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ይኸውም ተማሪዎች በውስን መጻፍ ደረጃ ካዳበሩት መሰረታዊ የዓረፍተነገር አጻጻፍ ክሂል በተጨማሪ የአጻጻፍ ስልትን ለመለየት የሚያግዙና ወደ ነጻ (Free writing) የሚያሸጋግሩ ይዘቶችን የሚይዝ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች መምህሩ በሚቀርብላቸው ሞዴል መሰረት የመጻፍ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ መምህሩ ሞዴሉን መሰረት እያደረገ የሞዴሉን አገልግሎትና የአጻጻፍ ስልቶች በመግለጽ፣ ምሳሌ በማሳየት፣ የቀረበውን ሞዴል አንብበው ባህርያቱን እንዲገመግሙ በማድረግ መጠነኛ በሆነ ልዩነት ተመሳሳይ ጽሁፍ እንዲጽፉ ያበረታታል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚካሄዱ ውይይቶች ድርሰትን ለመጻፍ የሚያገለግሉ ምር የመጻፍ ተግባራት መሆናቸውን Raimes (1983) ይገልጻሉ፡፡

**ሐ. ነጻ (ልቅ) መጻፍ፡-** በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በአብዛኛው መምህሩ በሚሰጣቸው ወይም ራሳቸው በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ሀሳብ አፍልቀው በራሳቸው ቋንቋና አገላለጽ ድርሰት የሚጽፉበት ነው (Raimes 1983)፡፡ ድርሰት የመጻፉ ስራ የሚጀምረው የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ቅርጾች በመለማመድ ነው፡፡ ከልምምድ ቀጥሎ ለሚጽፉት የድርሰት ዓይነት ሞዴል ይቀርባል፡፡ ሞዴሉን በአጻጻፍ ስልቱም ሆነ በይዘቱ መነሻ በማድረግ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ድርሰት እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡ ነጻ መጻፍ ለሰዋስዋዊ አጠቃቀምና ለስርዓተ-አጻጻፍ ትኩረት የሚሰጥ እንዲሁም በትክክለኛነት ላይ የሚያተኩር ቢሆንም ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ የሚገልጹበትን እድል ይሰጣል (Raimes 1983):: ስለሆነም ይህ ደረጃ በአንጻራዊነት በርካታ የመጻፍ ተግባራት የሚከናወኑበት ነው፡፡

ነጻ መጻፍ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ለመግለጽ የሚጽፉበት ደረጃ ቢሆንም የጽሁፋቸው መለኪያ ምን፣ እንዴት፣ ለማንና ለምን ተጻፈ? የሚሉት ጥያቄዎች ሳይሆኑ ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያልበዙበት ጽሁፍ ማቅረብ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎቹ ትኩረት የሚያርፈው ሀሳባቸውን በመግለጽ ላይ ሳይሆን በጽሁፋቸው ጥራት ላይ ነው (Byrne 1991)፡፡

ውጤታዊ አቀራረብ ተማሪዎችን ከውሱን መጻፍ ወደ ነጻ የአጻጻፍ ልምድ እንዲሸጋገሩ ስለሚያደርግ ብዙ ጊዜ ለስህተት አያጋልጣቸውም፡፡ አብዛኛው ጊዜ ከትክክለኛ የአጻጻፍ ልምድ ጋር ስለሚያስተዋውቃቸው ምሳሌውን ተከትለው የራሳቸውን ትክክለኛ ዓረፍተነገር መመስረትና ሀሳብን በጽሁፍ ማስተላለፍ እንዲችሉ ያግዛቸዋል (Richards 1990)፡፡ ነገር ግን በዚህ ዘዴ የሚማሩ ተማሪዎች ሁልጊዜ የተጠናቀቀ ነገርን ብቻ እንዲጠቀሙ ስለሚያደርግ

በመጻፍ ክሂል ትምህርት ሂደት የሚታለፍባቸውን ማቀድን፣ ማርቀቅን፣ መከለስንና ማረምን የዘነጋ መሆኑን Raimes (1983) በመጠቀም ደካማ ጎኑ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

### 2.6.1.2 በውጤት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት የመምህሩ ሚና

በውጤት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የመምህሩ ሚና በአብዛኛው የቋንቋውን ሰዋስውና ህጎችን ማስተማር የተማሪዎችን የመጨረሻ ውጤት ሰብስቦ ሰዋስዋዊ ስህተቶችንና የአጻጻፍ ግድፈቶችን ማረም፣ የጽሁፉን ጥሩነትና መጥፎነት ከትክክለኛነት አንጻር መገምገም፣ ለመማር የሚያበረታታ አስተያየት ወይም ውጤት መስጠት ነው፡፡ በውጤት-ተኮር አቀራረብ መጻፍን ለማስተማር የሚዘጋጅ መምህር ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ተገቢውን ዝግጅት ሊያደርግ እንደሚገባ Byrne (1988) የሚከተሉትን ነጥቦች በመዘርዘር ይገልጻሉ፡፡

1. ለመጻፍ ክሂል የተመረጡት መልመጃዎች ለተማሪዎች ቀርበው ከመተግበራቸው በፊት ተገቢነታቸውን፣ ቀስቃሽነታቸውን፣ ግልጽነታቸውንና ለአውዱ ተገቢ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡
2. መልመጃዎቹ ግልጽ መመሪያ ያላቸውና ከሌሎች ክሂሎች ጋር ቅንጅት ያላቸው መሆኑን ያሳውቃል፡፡
3. የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት ለተማሪዎች በማሳወቅ በጽሁፋቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡
4. ተማሪዎች ለመጻፍ ትምህርት ቅድመ-ዝግጅት የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
5. የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እየተከታተለ ደረጃውን ጠብቆ ተገቢ መልመጃዎችን በማዘጋጀትና በማለማመድ ለምሳሌ ከውስን መልመጃ ወደ ምር የመጻፍ ደረጃ አሸጋግሮ ከዚያም ከምር ወደ ነጻ የመጻፍ ደረጃ ያሳድጋል፡፡
6. በተሰጣቸው መመሪያ ወይም ሞዴል መሰረት ጽፈው እንዲመጡ በማድረግ ተማሪዎችን በየደረጃው ይመራል፤ ይቆጣጠራል፡፡
7. መልመጃዎችን በግል፣ በጥንድና በቡድን ለማሰራት በሚያስችል መልኩ በማዘጋጀት ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ያሰራል፡፡
8. ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ከጻፉ በኋላ ስራዎቻቸውን ተለዋውጠው እንዲተራረሙና አስተያየት እንዲሰጡ ያበረታታል፡፡

9. በመጨረሻም የተማሪዎችን ጽሁፍ በማንበብ በጽሁፉ ማጠቃለያ ላይ አስተያየት ይሰጣል (Kroll 1991)::

### 2.6.2 ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ምንነት

ማንኛውም ሰው የመጀመሪያ ቋንቋውን ያለምንም ችግር መናገር ሲችል መጻፍን ግን ትምህርት ቤት ገብቶ ይማረዋል፡፡ ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴ ብዙና የተሸሉ ብልሀቶችን ስለሚጠቀም የመጻፍ ክሂልን በማጎልበት ረገድ የተሻለ እንደሆነ Raimes (1983) ያስረዳሉ፡፡ ይህ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በውስጡ ቅድመ-መጻፍ፣ ማረቀቅ፣ መከለስ፣ አርትኦት ማድረግ የሚባሉ ሂደቶችን እንደሚያጠቃልልና እነዚህን በአግባቡ መጠቀም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እንደሚያጎለብት Silva (1990) ይገልጻሉ፡፡

ይህ አቀራረብ ውጤት ላይ ለመድረስ የሚከናወኑ ሂደቶችን መሰረት የሚያደርግ መሆኑን Raimes (1983) ያስረዳሉ፡፡ በዚህ አቀራረብ ከትክክለኛነት ይልቅ የአጻጻፍ ሂደት ትልቅ ግምት ይሰጠዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የራሳቸውን ርዕስ እንዲመርጡ፤ ሀሳብ እንዲያመነጩ፤ እንዲያደራጁ፤ አስተዋጽኦ መንደፍ እንዲችሉ የጻፉትን ለጓደኛ ወይም ለመምህር በመስጠት እንዲያሳርሙና የተሰጣቸውን ማስተካከያ ተቀብለው እንደገና በማስተካከል ዋናውን ጽሁፍ እንዲያቀርቡ የሚያደርግ ነው፡፡ እንደ Byrne (1991) አመለካከት ሂደታዊ የመጻፍ አቀራረብ መጻፍ በተፈጥሮው ሂደት ነው የሚል እሳቤን ያነገበ ነመሆኑ መጻፍ ተመላላሽ ወይም ዙር መጥ ተግበባራትን የያዘ ነው፡፡ ስለሆነም ጸሀፊው ወደፊትና ወደኋላ በመመላለስ የመጻፍ ተግባርን ሊያከናውን ይችላል፡፡

ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ለመጻፍ የተመረጠውን ርዕስ በተመለከተ ሀሳብን በዝርዝር ማስፈር፣ አስተዋጽኦ መንደፍ፣ ረቂቅ ማዘጋጀት፣ ረቂን መንደፍ፣ ረቂቅ ማዘጋጀት፣ ረቂቁን መጻፍ ረቂቁን ማስተካከልና ማሻሻል እንዲሁም የመጨረሻውን ረቂቅ መጻፍን ይይዛል፡፡

ሰለሞን ዮሃንስና ሌሎች (1994) Donald Muley (1982) ን ጠቅሰው እንደገለጹት ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴ በሶስት ደረጃዎች ውስጥ እንደሚያልፍ ያመለክታል፡፡ ብዙዎች ጸሀፊዎች የሚጠቀሙበት የአጻጻፍ ዘዴ ነው፡፡ የታሰበበት የመጻፍ ስራ ወደኋላ ተመልሶ ሳይታይ እንደተጀመረ ቀጥሎ አንድ ቦታ ሲደርስ የሚያበቃ አይደለም፡፡ የጻፍነው ጽሁፍ ወደተደራሲ ከመድረሱ በፊት መላልሰን የምንመለከተው መሆን አለበት፡፡ ሂደታዊ ጽሁፉን ተግባር

ለተማሪዎች ማስተዋወቅንና ማለማመድን ብሎም መከታተልንና ማቃናትን ይመለከታል፡፡ በዚህ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች የጽሁፍ ስራቸውን ከላይ እንደተጠቀሰው በሶስት ደረጃዎች ውስጥ እንዲያሳልፉ ይጠበቃል፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

**ሀ. የቅድመ-መጻፍ ደረጃ፡-** በዚህ ደረጃ ርዕስ የሚመረጥበት፣ የሚጠብበት፣ እና ሀሳብ ከሰው ከመጽሀፍት የሚሰበሰብበት ነው፡፡የተሰበሰበውም ሀሳብ በቅደምተከተል የሚደራጅበት ነው፡፡ ይህ ደረጃ ስለርዕሱ ስለሚጻፍበት ዓላማ፣ ስለተደራሲው ማንነት የሚያሰላስልበት ነው፡፡

**ለ. የመጻፍ ደረጃ፡-** በዚህ ደረጃ በቅድመ-ጽህፈት ደረጃ ጸሀፊው ያሰበበትን ነገር መሰረት አድርጎ በቅደምተከተል ያደራጀውን ሀሳብ የሚጽፍበት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ስለሀሳብ ተትክክለኛነት ስለስርዓተነጥብ ስለቃላት፣ ስለዓረፍተነገር፣ አንቀጽ… ዝርዝር ነገሮች ትኩረት የሚደረግበት አይደለም፡፡ በአስተዋጽኦ እየተመሩ ዝም ብሎ የሚጻፍበት ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች ጸሀፊው ለወደፊት ሊያስተካክላቸው ስለሚችል ነው፡፡

**ሐ. ድህረ--መጻፍ ደረጃ፡-** ይህ ደረጃ በመጻፍ ደረጃ የተጻፈውን ጽሁፍ ጸሀፊው ተመልሶ የሚመረመርበትና  የሚያስተካክልበት ነው፡፡ በድህረ-መጻፍ ደረጃ ጸሀፊው ስለጽሁፉ ይዘት የሃሳብ አደረጃጀት፣ ስለቃላት፣ ዓረፍተነገር፣ አንቀጽ፣ ስርዓተነጥብ፣ ስለተደራሲው የጽህፈት ባህሪ እያሰበ የሚጽፍበት ይሆናል፡፡ ጸሀፊው በዚህ የመጻፍ ደረጃ ላይ እያለ ወደቅድመ-መጻፍና የመጻፍ ደረጃ እየተመለከተ እንደገና ደግሞ ወደደረረሰበት የመጻፍ ደረጃ እየሄደ ይጽፋል፡፡ የአጻጻፉን ስልት ሂደታዊ የሚያሰኘውም  ይኸው ወደፊትና ወደኋላ እያሉ መጻፍ ነው፡፡ በዚህ የአጻጻፍ ስልት ወደፊትና ወደኋላ እየተባለ ሲሰራ ሀሳብ እንዴት ግልጽ ሊሆንና ሊጠራ እንደሚችል ያሳያል፡፡

ሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ እንደውጤታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ በተጠናቀቀ የድርሰት ረቂቅ ላይ እንዲሁም በቋንቋው ቅርጽ ላይ ከማተኮር ይልቅ በመፍጠር፣ አዲስ ነገር በመፈለግና ትርጉምን የማስፋት ሂደትን የሚከተልና በጽሁፍ ይዘት (ፍች) ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የመምህሩ ሚና ከውጤት ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተለየ ነው፡፡  ይኸውም ተማሪዎቹ አንድን ጽሁፍ ለመጻፍ ደረጃ በደረጃ የሚያከናውኑት ተግባር ሀሳብን ማፍለቅና ማደራጀት ማርቀቅ በተደጋጋሚ ረቂቅ መጻፍ መከለስ፣ መሰረዝ፣ መጨመር፣ መቀነስና ደጋግሞ ሀሳብን ማደራጀት ለማረም የቃላት መረጣን፣ የዓረፍተነገር አወቃቀርንና የአጻጻፍ ስርዓትን መከተልና መረዳት ላይ የሚያተኩሩ

ከመሆኑም በተጨማሪ ተማሪዎች የራሳቸውን ስትራቴጅ እንዲያዳብሩ የማስቻል ሚና አላቸው (Hedge 1988):: ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ለማስተማሪያነት ስለማገልገሉ የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ቀጥለን ስንመለከት Raimes (1983) እንደሚሉት በዚህ ዘዴ የሚያስተምሩ መምህራን ሁለት ወሳኝ የሆኑ ድጋፎችን ለተማሪዎቻቸው መስጠት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎች በሚሰሯቸው ረቂቆች ላይ ሀሳብ ማመንጨት እንዲችሉና የይዘት ምጋቤ ምላሽ እንዲያገኙ ጊዜ ይሰጧቸዋል፡፡ ሁለተኛው የመጻፍ ሂደት የመፍጠር ሂደት እንዲሆንላቸው ተማሪዎቻቸውን ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡

Trayka (1990) በበኩላቸው የአጻጻፍ ሂደትን ለማስረዳት ያህል ለየብቻ በየደረጃው የሚከናወኑትን የተለያዩ ተግባራት ጽሁፉ እያደገ ሲሄድ በተግባር እንደሚታየው የአጻጻፍ ደረጃዎቹ አንዳቸው በሌላኛው ውስጥ ገብተው እንደሚገኙ ይገልጻሉ፡፡ እነዚህንም ደረጃዎች እንደሚከተለው ያቀርቧቸዋል፡፡ እነሱም፡-

1. የማቀድ ደረጃ ስለርዕሠ-ጉዳይ ትኩረት የሚደረግበትና ሀሳብ የሚሰበሰብበት ነው፡፡
2. ማደራጀት የተሰበሰቡ ሀሳቦችን ማቀናጀት ይመለከታል፡፡
3. ማርቀቅ በተቀናጀው ሀሳብ መሰረት ሀሳብን በዓረፍተነገሮችና አንቀጾች ማስፈር፡፡
4. መከለስ ረቂቁን መገምገምና እንደገና መጻፍን ይመለከታል፡፡ በዚህ ደረጃ መጨመር፣ መቀነስ፣ መሰረዝ፣ ቦታን ማቀየያየር ወዘተ ይኖራል፡፡
5. አርትኦት የተከለሰውን ስራ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነቱን ማየት፣ የፊደል ጉድለትን ስርዓተነጥቦችንና አደረጃጀቱን መመልከቻ ደረጃ ነው፡፡

በተጨማሪም Murray Danise (1992) የሂደት-ተኮር አጻጻፍን ምንነት በተመለከተ ሲገልጹ ሂደት-ተኮር የአጻጻፍ ዘዴ በአንድ አቅጣጫ ወደፊት በዘፈቀደ የመገስገስ ሂደት ሳይሆን ራሳቸውን የቻሉ ቃላትንና ሀረጎችን በወረቀት ላይ በመጻፍ፣ ከተጻፉት ቃላትና ሀረጎች በመነሳት ጸሀፊው ለማስተላለፍ የፈለገውን መልእክት ማዳበርን ይጠይቃል ይላሉ፡፡

በተጨማሪም ይህ የአጻጻፍ ዘዴ የመማር ማስተማሩ አውድ አዎንታዊ፣ አበረታችና ትብብራዊ አሰራር በሚታይ መልኩ ተማሪዎች በራሳቸው የመማር ፍጥነት በተወሰነ የመምህር ጣልቃ ገብነት እንዲለማመዱ እድል የሚሰጥ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነ Silva (1990) ይገልጻሉ፡፡ በአጠቃላይ ዘዴው ተመራማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጽፉትን ርዕስ እንዲመርጡ፣ በመረጡት ርዕስ ላይ በጥንድ፣ በህብረት እየሆኑ

እንዲወያዩ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር እየሆኑ እንዲተራረሙ፤ ባገኙትም እርማት ጽሁፋቸውን በተደጋጋሚ እንዲያሻሽሉ የሚያበረታታ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 2.6.2.1 የሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ አስፈላጊነት

ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴን በመጠቀም መጻፍን ማስተማር የራሱ የሚተችባቸው ነጥቦች ያሉት ቢሆንም በመጻፍ ክሂል ላይ መሰረታዊ ለውጥ ያመጣ እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ለውጡም የተማሪዎችን ሚናና የመምህሩን ሚና በአጠቃላይ በመጻፍ ማስተማሪያ ክፍል የማስተማር ሂደት ላይ በተማሪዎች መካከል እርስ በርስ ተባብሮ የመስራት ሁኔታ እንዲኖር የሚያበረታታ ነው፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች የመጻፍ ተግባራትን ለመጀመር የሚችሉበትን ሁኔታ ማለትም ርዕስ መምረጥ፣ ሀሳብ ማመንጨት፣ እቅድ ማዘጋጀት የሚባሉትን ሂደቶች እንዲያበለጽጉ እንዲሁም የማርቀቅ፣ የመከለስ ሂደቶችንና አርትኦት የመስጠት እውቀቶችን የማሳደግ ሚና እንዳለው Silva (1990) ያስረዳሉ፡፡

ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴ አዲስ ነገር የመፈለግ፣ ትርጉም የማስፋት ሂደትን የሚከተልና በጽሁፍ ይዘት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በዚህ ዘዴ አንድን ጽሁፍ ለመጻፍ ደረጃ በደረጃ የሚያከናውኑት ተግባራት ሀሳብን ማፍለቅና ማደራጀት፣ ተደጋጋሚ ረቂቅ መጻፍ፣ መከለስና ደጋግሞ ሀሳብ ማደራጀት፣ የቃላት መረጣን፣ የዓረፍተነገር አወቃቀርንና የአጻጻፍ ስርአትን መከተልና መረዳት ላይ የሚያተኩር ከመሆኑም በተጨማሪ ዘዴው የራሳቸውን ስትራቴጅ እንዲያዳብሩ የማስቻለል ጠቀሜታ እንዳለው ያስረዳሉ (Silva 1990)፡፡

ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴ ተማሪዎች ከመጻፊያ ጊዜ አንስቶ እስከማጠናቀቂያ ጊዜ ከጓደኞቻቸውና ከመምህራን ጋር በሚያገኙት አስተያየት የመጻፍ ክሂላቸውን ለማዳበር በእጅጉ አስተዋጽኦ እንዳለው ይገልጻሉ (Kroll 1990)፡፡ ተማሪዎች አንባቢን የጽሁፉን ይዘት ሰዋሰውንና ሌሎችን በቀጥታ ለየብቻ ትኩረት እንዲሰጧቸው ከማድረግ ይልቅ ከተማሪዎችና ከመምህራን የሚያገኟቸው አጠቃላይ አስተያየቶች ለጽሁፍ ክሂላቸው መዳበር አስተዋጽኦ እንዳለው ነው፡፡

በ Leki (1996) አገላለጽ ሂደታዊ የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ከሌሎች ዘዴዎች ይልቅ ተማሪዎች በመወያየት፣ ሀሳብ በመለዋወጥ ትምህርታቸውን እንዲማሩ የሚያስችላቸው በመሆኑ ተመራጭ መሆኑን አስምረውበታል፡፡ ምክንያቱም ዘዴው ከመጀመሪያው የመጻፍ ደረጃ እስከ እስከመጨረሻው ጋር ተማሪዎች ጽሁፋቸውን በመወያየትና ሀሳብ በመጋራት ወዘተ አደራጅተው እንዲጽፉና የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብብሩ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

ይህ አጻጻፍ ዘዴ ቅድመ-መጻፍን፣ ማርቀቅን፣ መከለስንና አርትኦት የማድረግ ሂደትን ይይዛል፡፡ እነዚህን በአግባቡ መጠቀም የመጻፍ ችሎታን ያጎለብታል፡፡ በአጠቃላይ ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴ ተማሪዎች በጽህፈት አማካኝነት ሀሳባቸውን በማብላላት፣ ጽሁፎቻቸውን ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በመተባበር የሚጽፉበትን ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርና ስለስራቸው በእያንዳንዱ የመጻፍ ደረጃ የተለያዩ ጠቃሚ አስተያየቶችን ከመምህራን እና ከጓደኞቻቸው እንዲያገኙ እድል በመስጠቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡

በቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች የተሻለ የሚባል አንድ ወጥ የማስተማሪያ ዘዴ ለመምረጥ አዳጋች መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ነገር ግን ከላይ በቀረበው ገለጻ ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪው የሂደቱ ዋነኛ አካል በመሆኑ ንቁ ተሳታፊ በማድረግ በጽሁፍ ጊዜ የተማሪው የቀደመ እውቀት ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት የሚያምን ሲሆን አጠቃላይ አቀራረቡም መጨረሻ ላይ ከሚገኘው ውጤት ይልቅ ጽሁፉ ለሚካሄድበት ሂደት ትኩረት ያደርጋል፡፡

የሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዓላማው የጸሀፊዎችን ሀሳብ መገንዘብና መግለጽ እንዲሁም የመጻፍ ክሂልን ማሳደግ ላይ ትኩረት ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህን የመጻፍ ትምህርት አቀራረብን ውጤታማነትና በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና ለመረዳት  አጥኝው በሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሚፈጥረውን ለውጥ ለማረጋገጥና ተግባር ላይ ለማዋል ጥናቱን ያካሂዳል፡፡

### 2.6.2.2 የሂደት-ተኮር አጻጻፍ ዘዴ ቅደም-ተከተላዊ ደረጃዎች

በሂደት-ተኮር አቀራረብ መጻፍን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ልዩ ልዩ የመጻፍ ደረጃዎችን ያልፋሉ፡፡ Richards (1990) በሂደታዊ ዘዴ መጻፍን ለማስተማር የተለያዩ የክንውን አይነቶችን መንደፍ እንደሚያስፈልግ ይነግሩናል፡፡ በተጨማሪም Murray (1982) የሂደታዊ አቀራረብ ዘዴ የአጻጻፍ ሂደት በሶስት ደረጃዎች እንደሚያልፍ ያሳዩናል፡፡ እነዚህም፡-

**ሀ. የማሰላሰል ደረጃ** (Rehearsing Phase)፡- የማሰላሰል ደረጃ የቅድመ-መጻፍ ደረጃ ሲሆን መጻፍ ከመጀመር በፊት የሚከናወኑ ዝግጅቶችን በሙሉ ይይዛል፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ሀሳባቸውን የሚሰበስቡበት፣ ርዕስ የሚመርጡበት፣ ስለሚጽፉት ርዕሰ-ጉዳይ የተለያዩ ሀሳቦችን ከተለያየ አቅጣጫ የሚሰበስቡበት፣ ዕቅዳቸውን የሚነድፉበትና በአጠቃላይ ወደዋናው

የመጻፍ ደረጃ ለመግባት የሚዘጋጁበት ሂደት ነው፡፡ ስለምን ልጻፍ እና እንዴት ልጻፍ የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙት በዚህ ክፍል ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በመረጡት ርዕስ ላይ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ይነጋገራሉ፡፡ መምህራን ለተማሪዎች መመሪያ በመስጠት የሚጽፉትን ርዕሰ-ጉዳይ በሚገባ እንዲያውቁ ይመራሉ፤ ይከታተላሉ (Richards 1990)፡፡

**ለ. የማርቀቅ ደረጃ** (Drafting Stage)፡- ይህ ደረጃ በመጻፍ ጊዜ የሚከናወን ተግባር ሲሆን በዚህ ደረጃ ሀሳብ በማፍለቅ ጊዜ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የማመቻቸትና የመጀመሪያ ረቂቅ መጻፍ፣ የተጻፈውን የማንበብና የመከለስ ጽሁፉ የሚዳብርበትን ሀሳብ የመፈለግ ተግባር የሚከናወንበት ነው፡፡ ተማሪዎች በዚህ ጊዜ ለሰዋስዋዊ ስህተት አይጨነቁም፤ ሀሳብ እንደመጣላቸው ይጽፋሉ፤ የማይፈልጉትን ሀሳብ አውጥተው አዲስ ሀሳብ መተካት ይችላሉ፡፡ በዚህ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጠው ለይዘት ትክክለኛነት ሲሆን በቀጣይ በሚጽፉት የድርሰት ረቂቅ ላይ ከይዘት ባሻገር ተማሪዎች የተጠቀሙባቸውን ሥርአተነጥቦች፣ ሰዋስዋዊ ስርዓቶች የሆሄያት አጣጣልን ወዘተ የመመርመርና የማስተካከል ተግባርን ያከናውናሉ (Hedge 1991)፡፡ በዚህ ደረጃ ጸሀፊው ያረቀቀውን ሀሳብ መግቢያ፣ ዋና አካልና መደምደሚያ በማለት ያከፋፍላሉ፡፡

**ሐ. የክለሳ ደረጃ** (Revising Stage)፡- ከተደራሲ አተያይ አኳያ የመልዕክቱን ግልጽነት የሚገመግምበት ጽሁፉን በማንበብ ለአንባቢ መቅረቡን የሚያረጋግጥበት ክንውን ነው፡፡ በዚህ ደረጃ የመጨረሻ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡ ጽሁፉ ለአንባቢ ሊጠቅም የሚችልና ትክክለኛ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

እነዚህን ሂደቶች ማስተማሩ ወይም መማሩና ክሂሉን ማዳበሩ ለጽሁፍ ተግባቦት ብቃት የራሱ የሆነ ድርሻ አለው፡፡ ይሁን እንጅ በአጻጻፍ ሂደት በማለፍ በሚዳብሩ ስነ-ልሳናዊ ክሂሎች ብቻ መግባባት ይቻላል ማለት አጠያያቂ ይመስላል፡፡ ተማሪዎች ከአጻጻፍ ስልትና ከጽሁፍ አደረጃጀት ጋር ሳተዋወቁና ሳይለማመዱ በማሰላሰል፣ በማርቀቅነ፣ በመከለስና በማረም ሂደት በማለፍ ብቻ የተሟላ የጽሁፍ ቅርጽ እንዲጽፉ፣ በጽሁፍ እንዲግባቡ፣ መጠየቅ የማይቻል ይመስላል፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎችን የሂደታዊ አጻጻፍ የሂደት ደረጃዎችን በጠበቀ መልኩ ድርሰት ጻፉ የሚል ትዕዛዝ ማስተላለፍ ሳይሆን ተማሪዎች የተዋጣለት ድርሰት መጻፍ እንዲችሉ ሂደቱን እንዲተገብሩ ማበረታታት የተሻለ ይሆናል፡፡

### 2.6.2.3 በሂደት-ተኮር አቀራረብ የመምህሩ ሚና

በሂደታዊ አቀራረብ መጻፍን የሚያስተምር መምህር ለተማሪዎች የእርስ በርስ መማማር ቦታውን እንደሚለቅ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም መሰረት መምህሩ የመማር ሁኔታን የሚያመቻችና የመከታተል፣ የተማሪዎችን የመጻፍ ተግባቦታዊ ክሂሎች የማዳበር፣ የተማሪዎችን የመጻፍ ተግባቦታዊ ክሂሎች የማዳበር፣ የተማሪዎችን ጽሁፍ የማንበብ፣ የመገምገምና በመመካከር እንዲማሩ የማገዝ እና መማርን የማፋጠን ሚና ይጫወታል (Rudder 1999)፡፡

በአጻጻፍ ሂደትም ተማሪዎች በማሰላሰል፣ በማርቀቅ፣ በማቀድ፣ በመከለስ ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜም የመምህሩ ሚና ለተማሪዎች የሚጽፉበተትን ምቹ ሁኔታ ማዘጋጀት፤ በቂ ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ፤ … ይጠቀሳሉ፡፡

ሂደታዊ የመጻፍ አቀራረብ በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ የመምህሩ የማስተማር ዘዴ በተመለከተ የሚከተለውን ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡ በሂደታዊ አቀራረብ መምህሩ ተማሪው እንደ ውጤታዊ አቀራረብ ዘዴ ያለቀለት ስራ እንዲያቀርቡ የተወሰነ ነገር የሚጠይቅ ሳይሆን ተማሪው ትክክለኛ ጽሁፍ ለመጻፍ የሚያስችለውን ዘዴ የሚቀይስና የሚያመቻች እንደሆነ ይገልጻሉ (Richards 1990)፡፡

በሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ወቅት የመምህሩ ሚና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ምን መሆን እንዳለበት Richards (1990) የሚከተሉትን ነጥቦች ይዘረዝራል፡፡

1. የመጻፍ ስራ ግልጽ ቀላልና ቀጥተኛ እንዲሆን በማድረግ የአጻጻፍ ሂደቱን ያስተምራል፡፡
2. የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የሚያስችል የአጭርና የረዥም ጊዜ ግብ ያዘጋጃል፡፡
3. የድርሰቱን ውጤት ይተነትናል፤ ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ይሆናሉ ብሎ የሚያስባቸውን ሀሳቦች ይጠቁማል፡፡
4. የክፍል ውስጥ ክንውንን በግልና በቡድን እንዲሰሩ በማከፋፈል የክፍሉን ተማሪ በእኩል ተሳታፊ ያደርጋል፡፡
5. ተማሪዎች እርስ በርስ የሚማሩበትን አመች ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
6. ተማሪዎች በመጻፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ ሀሳባቸውን በተለያየ መንገድ እንዲያፈልቁ ያግዛል፡፡

7. ተማሪዎች የተለያዩ አስተሳሰቦችንና የሀሳብ ቅደምተከተሎችን በተገቢው መንገድ መጻፍ የሚችሉበትን የድርሰት አጻጻፍ ህጎችን ያስተምራል፡፡
8. ተማሪዎች በመጻፍ ሂደት ላይ ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

### 2.6.2.4 በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪው ሚና

በሂደታዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪው ዋነኛ ሚና መማር ነው፡፡ መማርን ማከናወን ያለበትም የነገሩትን በሙሉ በማድረግና የሰጡትን ሳይጠይቅ በመቀበል ሳይሆን በመስራት፣ በመመርመር፣ በመሞከርና በማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም በተማሪው የመማርሚና ላይ የሚከሰተው ልዩነት ሌተማሪው ከሚሰጠው ትኩረት የሚመነጭ ሲሆን በመማሩ ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር መገመት ይቻላል፡፡

የተማሪው ሚና ለመማር ሂደት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በማስተማር አቀራረቦችና ስነዘዴዎች ውስጥ በግልጽም ሆነ በውስጠ-ታዋቂነት ይታያል፡፡ ይህም በትምህርቱ ሂደት ተማሪው በሚያከናውናቸው ተግባራት አይነቶች፣ ለትምህርት በሚቀርበው ይዘት ላይ የሚኖረው ተነሳሽነትና በሚሰራበት ቡድን ውስጥ ባለው ተሳትፎ ሊገለጽ ይችላል (Richards & Rodgers, 1986)፡፡

ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የመጻፍ ትምህርት ከውጤት-ተኮር ወደ ሂደት-ተኮር መለወጡን ተማሪዎች በሚያከናውኗቸው ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረጉን ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ Richards (1990), Zamel (1987)ን በመጥቀስ በሂደት-ተኮር አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች ምን መጻፍ፣ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው ትኩረት የመስጠትና የራሳቸውን የጽሁፍ ስራ ራሳቸው በማረም ተሳትፎ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይገልጻሉ፡፡ በመማሩ ሂደትም ተማሪዎች የሚጽፉበትን ርዕስ ይመርጣሉ፤ በህብረት እንዲጽፉም ይበረታታሉ፡፡ በዚህ ሂደትም ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተራክቧዊ አሰራርን ያዳብራሉ፡፡ ርዕስን ከቤትና ከትምህርት ቤት ገጠመኞቻቸው በመምረጥ በህብረት በሚጽፉበት ጊዜ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የሚያወቋቸውንና የሚጠቀሙባቸውን ነገሮች በምንጭነት ይጠቀማሉ፡፡ ይህ በእውናዊና በራስ ገጠመኝ ላይ መጻፍ የመማር ተነሳሽነትን ለማጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ ጎበዝና የትምህርቱ ሂደት ደከም ያሉ ተማሪዎች በመተጋገዝ እንዲሰሩ የሚያጋጥሙ ችግሮችንም በጋራ እንዲፈቱ ያስችላቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በሂደት-ተኮር አቀራረብ ዘዴ መጻፍን መማር ተማሪዎች በራሳቸው የመማር ሀላፊነትን የመውሰድ፤ የብዙ ሰዎችን አስተያየት የመጠቀምና በመጻፍ አማካኝነት ሀሳብን የመሰብሰብ … ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ የራሳቸውን እውቀት በራሳቸው ቋንቋ ለመግለጽ የማሰላሰል፣ የማቀድ፣ የመወያየት፣ ለማንና ለምን እንደሚጽፉም የመወሰን፣ ረቂቅ የመጻፍ፣ የመከለስና የማረም ሂደቶችን ያከናውናሉ፡፡

### 2.6.2.6 በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ለተማሪዎች የሚሰጥ ምጋቤ-ምላሽ

ተለምዷዊ በሆነው የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ጽሁፎች ምጋቤ-ምላሽ የሚሰጡት መምህራን ናቸው፡፡ በጽሁፉ ውስጥ የተካተቱትን ስህተቶች ለቅመው በማውጣት ምጋቤ-ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ይህ አይነቱ የአሰራር ሂደት ሁለት ችግሮች እንደሚኖሩት Zamel (1992) ይገልጻሉ፡፡ የመጀመሪያው በጽሁፍ ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም ችግሮችን ፈልጎ አንድ በአንድ ለማረም ለመምህራን አስቸጋሪ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ብዛት ያለውን እርማት ተማሪዎች መለካት የመሰላቸትና ተስፋ የመቁረጥ ነገር ሊያስከትል እንደሚችል ነው፡፡

እነዚህ አብይ ችግሮች ለመወጣት የተማሪዎችን የጽሁፍ ውጤት ከማረም ገና በሂደቱ ላይ ተከታታይ ማስተካከያ መስጠት ተመራጭ መሆኑንና እንዲህ አይነቱ ማስተካከያ ተማሪዎች ስሜታቸው ተነሳስቶ በመጻፍ ሂደት ላይ እያለ ስለሚሰጥና የወዲያውኑነት ባህርይ ስላለው የመጻፍ ሞራላቸውን አይነካም፡፡ ስለዚህ በእያንዳንዱ ሂደታዊ የአጻጻፍ ደረጃ ምጋቤ-ምላሽ መስጠትና ተማሪዎች ሲጽፉ የሚያስቸግሯቸውን ለቅሞ በማውጣት የሚማሩበት ሰሌዳ ላይ ማሳየት የተማሪዎችን የጽሁፍ ስህተት ይቀንሳል፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እንደሚያጎለብትና ለመጻፍ ያላቸውን ፍላጎት እንደሚያነሳሳ Zamel (1992) ይገልጻሉ፡፡

በጽሁፍ ላይ ምጋቤ-ምላሽ መስጠትን አስመልክተው ተማሪዎቹ ተጽፎ ባለቀው ጽሁፍ ላይ ይሰጥ ሲሉ መምህራን ደግሞ ገና በሂደቱ ላይ እያለ ይሰጥ የሚል ምርጫ አላቸው፡፡ ለዚህም ጽሁፍ በሂደት ላይ እያለ ምጋቤ-ምላሽ መስጠቱ ጠቃሚነት እንዳለው ገልጸው አስፈላጊነቱም በውጤቱ ላይ የሚሰጠው ምጋቤ-ምላሽ ለሚቀጥለው ጽሁፋቸው ብቻ አስፈላጊ ሲሆን በሂደቱ ላይ የሚሰጠው ምጋቤ-ምላሽ ጠቀሜታ ግን እየተጻፈ ላለውም ሆነ ለቀጣዩ ጽሁፍ  እንደሆነ ያስረዳሉ (Zamel 1992)፡፡

## 2.7 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር የሚዳሰሱት ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ዝምድና ያላቸው የአገር ውስጥ ቀደምት ጥናቶች ናቸው፡፡ በዳሰሳው ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች ከዚህ ጥናት ጋር በርዕስ፣ በዓላማ፣ በአጠናን ዘዴና ከውጤት ትንተና አንጻር ባሉት ተመሳስሎዎችና ልዩነቶች ላይ ሲሆን ከነዚህ ነጥቦች አንጻር የሚከተሉት ስራዎች ተቃኝተዋል፡፡

አማረ (2010) ተግባር-ተኮር የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽእኖ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማም በተግባር-ተኮር ዘዴ ቋንቋን ማስተማር በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ከመፈተሽ በተጨማሪ የተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መፈተሽ ነው፡፡

ዘላለም (2009) የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ትምህርትን የማጎልበት ሚና ትንተና በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ:- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሂደታዊ የጽህፈት ማስተማሪያ ስልቶችን በመተግበር የተማሪዎች የጽህፈት ክሂል በየትኛው የጽህፈት ማስተማሪያ ስልት ሊሻሻል እንደሚቻል መመርመር ነው፡፡ የመረጃ ትንተና ዘዴ አይነታዊና አሀዛዊ ስልት ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ፈተና፣ ሰነድ ፍተሻና ምልከታ ናቸው፡፡

ዳባሽ (2011)በሂደታዊ ዘውግ ማስተማር ዘዴ የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል ያለው ሚና በሰቃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ አፈ-ፈት በሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ ጥናታቸውን ያካሄዱ ሲሆን በማጠቃለያዋም በሂደት ዘውጋዊ የተማሩ የሙከራ ቡድኖች በተለምዷዊው የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ከተማሩ ተማሪዎች በተሻለ የመጻፍ ክሂላቸውን አሻሽለዋል የሚል ነው፡፡

ከላይ የቀረቡ ተዛማጅ ጥናቶች ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አይኑራቸው እንጅ ከቋንቋ ክሂሎች በመጻፍ ላይ በማተኮራቸው እንዲሁም የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ በማተኮራቸው ተመሳሳይነት ተስተውሎባቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ ለማጥናት

እንደተነሱበት ርዕሰ-ጉዳይ የጥናታቸው አነሳሽ ምክንያት፣ አላማ፣ ወሰን፣ እንዲሁም የአጠናን ዘዴ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ፣ የናሙና ሁኔታ… የተለያየ ነው፡፡

አለምነሽ (2011) ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴን በመጠቀም ጽህፈትን ማስተማር የጽህፈትን ክሂል በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና በሚል ርዕስ በ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ጥናታቸውን አካሂደዋል፡፡ በደረሱበት መደምደሚያም ሂደት ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ከተለምዷዊው በተሻለ መንገድ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ማዳበር እንደሚችል ይጠቁማል፡፡

አለምነሽ (2011) ጥናት ከላይ ከተጠቀሱ ጥናቶች በተለየ በርዕሱ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ መመሳሰል ቢኖረውም በፈተና ውጤት አያያዝ ግን ከዚህ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡ በአለምነሽ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ ለተማሪዎች የቀረቡ የፈተና ውጤቶች በደፈናው የመጻፍ ክሂል ይባል እንጅ እያንዳንዱ የተማሪዎች የመጻፍ ንኡሳን ክሂል ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በግልጽ አልተቀመጠም፡፡

ይህ ጥናት ደግሞ ከተማሪዎች ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና የተገኘውን ውጤት 10% ለስርአተ-ጽህፈት፣ 25 ለይዘት፣ 25 ለቋንቋ አጠቃቀም፣ 20 ለቃላትና 20 ለአደረጃጀት በመስጠት ለመተንተን የታቀደ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡ ሂደት-ተኮር የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና ከማጥናቱ በተጨማሪ ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ለማዳበር የሚኖረውን ሚና ከፅህፈት ንዑሳን ክሂሎች አንፃር ተንትኖ የሚያቀርብ በመሆኑ ከሌሎች ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማሻሻል  የሚኖረውን ሚና መፈተሽ ነው። ይህንንም ዋነኛ ዓላማ ለማሳካት አጥኚው ተግባር ላይ  ያዋለው አብይ የአጠናን ዘዴ መላምቶችን በመንደፍ መላምቶቹ ትክክል መሆን አለመሆናቸውን ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በተጠቀመው ፈተና አማካኝነት ማረጋገጥ ሲሆን የምርምር አይነቱም መጠናዊ ምርምር ሲሆን ከፊል ፍትነታዊ ዘዴን ተግባራዊ ያደረገ ነው። ከፊል ፍትነታዊ የምርምር ዘዴ ላይ የተመሰረተ በመሆኑም የቅድመና የድህረ-ትምህርት የፈተና ሂደትን ሊከተል ችሏል። ይህ ዘዴ ሁለት ተተኳሪ ቡድኖች የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተብለው ከመመደባቸው በፊት በወሰዱት ፈተናና  ከቅድመ-ፈተናው በኋላ በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሩ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች መካከል የሚያሳዩት የመጻፍ ክሂል ልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ የሚያመለክት ነው። አማረ Quasim (2014) ጠቅሶ እንደገለፀው የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና ስልት አንድ የማስተማሪያ ዘዴ ከፊል ፍትነታዊ በሆነ መልኩ ስራ ላይ በሚውልበት ጊዜ በሁለት ተተኳሪ ቡድኖች መካከል የታየ የውጤት ለውጥ ካለ የሚገመገምበት ነው።

ጥናቱ የሚከናወነው ተማሪዎቹ በሚገኙበት እውነተኛ አውድ (ክፍል) ውስጥ ሲሆን በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ በሶስት ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በተራ የእጣ ንሞና ሁለት ክፍል ተማሪዎችን ለቅድመ-ትምህርት ፈተና በመውሰድ ቅድመ-ትምህርት ፈተናውን በመፈተን ከልምምዱ በፊት ያላቸው የመጻፍ ክሂል ደረጃ ተፈትኗል። ከቅድመ ትምህርት ፈተናው በኋላ የሁለቱን ክፍል ተማሪዎች በተራ የዕጣ ንሞና ዘዴ አንደኛውን የሙከራ ሌላኛውን ደግሞ የቁጥጥር ቡድን በማድረግ ተመርጠዋል። ቀጥሎም የቁጥጥር ቡድን የደረሰውን በተለመደው የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የሙከራ ቡድኑን  ደግሞ በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በማስተማር በሁለቱ ቡድን መካከል ከቅድመ ትምህርት ፈተናው አንፃር ያለውን የመጻፍ ክሂል የውጤት ልዩነት መመርመር ተችሏል። በመጨረሻም በፈተና አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል።

## 3.2 የተማሪዎችና የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል በካፋ ዞን በአዲዮ ወረዳ ከሚገኙ ሰባት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመች ናሙና ተመርጧል፡፡ ይህ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው ላለፉት አምስት አመታት በዚሁ ትምህርት ቤት ሲያስተምር የቆየ በመሆኑ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅትም በማስተማር ላይ ስለሚገኝ በተቃራኒ ክፍለ ጊዜ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑን ተማሪዎች ለማስተማር በማስቻሉና ጥናቱ ከፊል ፍትነታዊ እንደመሆኑ መጠን የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ልዩ ትብብርና ሌሎች አስተዳደራዊ ድጋፎችን ማግኘት እንደሚችል ከግምት ውስጥ በማስገባቱ ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ ውስጥም ከ 9ኛ- 12ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአላማ ተኮር ናሙና በመምረጥ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ አስረኛ ክፍል በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ዘጠነኛ ክፍሎች ጥናቱ በተከናወነበት አመት ትምህርት ቤቱን የተቀላቀሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ ለጥናቱ ተገቢውን መረጃ ላይሰጡ ይችላሉ ብሎ በማሰቡ ነው፡፡ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ላይ ለሚመጡ ትምህርቶች ትኩረት የሚሰጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ አጥኚው የጥናት ጊዜያቸውን ላለመሻማት በማሰቡ የ10ኛ ክፍሎች በኣላማ ተኮር ናሙና ተመርጠዋል፡፡

በሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት 92 ተማሪዎች ሲሆኑ በሶስት ክፍል የሚገኙ በመሆናቸው ሁለቱን ክፍል ተራ የእጣ ንሞናን ተጠቅሞ በመምረጥ ቅድመ-ትምህርት ፈተና ተሰጧል፡፡ ከቅድመ-ትምህርት ፈተናው በኂላም ተራ የእጣ ንሞናን በመጠቀም አንዱን የቁጥጥር ሌላኛውን ደግሞ የሙከራ ቡድን በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ፈተና በመረጃ መሰብሰቢያነት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

ለተተኳሪዎች የሚሰጠው ፈተና በሁለት ግብ ላይ የተመሰረተ ነው እነሱም፡- በቅድሚያ የሚሰጠው ቅድመ-ትምህርት ፈተና የተጠኝዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃት ከልምምድ በፊት በውጤት ተቀራራቢ መሆን አለመሆናቸውን ለመገምገም ታስቦ የተሰጠ ፈተና ሲሆን ሁለተኛው (የድህረ-ትምህርት) ፈተናው ዓላማ ደግሞ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ የሚገመገሙበት ድህረ-ፈተና ሲሆን በተለምዷዊ የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሩትና

በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሩት ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ለውጥ ምን ያክል እንደሆነ ለመፈተሽ የተከናወነ ነው።

ቅድመ ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ፈተናዎቹ የተለያዩ ጥያቄዎች ሆነው ተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልቶችን የተከተሉ ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት ተመሳሳይ ጥያቄ ቢሆን ከቅድመ-ፈተናው በመነሳት ስህተታቸውን ለማስተካከል አመች ሊሆን ስለሚችል ነው። አማረ (2010) የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያቸውን በዚህ የአጠያየቅ ስልት ተጠቅመው ጥያቄዎችን ስላዘጋጁ ውጤታማም ስለነበሩ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍም ይህንን የአጠያየቅ ስልት በመከተል ፈተናዎቹ ተሰጥተዋል።

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አስተማማኝነትና ትክክለኛነት

በተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎች ውስጥ መረጃ ለመሰብሰብ የምንጠቀምባቸው የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አሉ። በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች አስተማማኝነታቸውን ለመፈተሽ የምንጠቀምባቸው የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ በርካታ ፀሀፍት ይገልፃሉ። ከዘዴዎች መካከልም የመለኪያ ይዘት ወጥነት፣ ዳግም ፈተና፣ ተመሳሳይ ይዘት መለኪያዎች … የሚጠቀሱ ናቸው (ያለው 2009)። ይሁን እንጅ ከላይ የተጠቀሱት የአስተማማኝነት መለኪያ ዘዴዎች ሁሉ ለሁሉም አይነት ላያገለግሉ ስለሚችሉ ተገቢውን የአስተማማኝነት መለኪያ መሳሪያ ለተገቢው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መጠቀም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም አጥኝው በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ በዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የሚጠቀመው ፈተና በመሆኑ ለዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ደግሞ ይዘታዊ ወጥነት የአስተማማኝነት መለኪያ ተግባር ላይ ውሏል። የቅድመና የድህረ-ትምህርት ፈተናው ውጤት የሁለቱ አራሚዎች የስምምነት ደረጃ በክሮንባች አልፋ ተፈትሿል።

የትክክለኛነት ምንነት ያለው (2009) ሲገልጹ ትክክለኛነት በአንድ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ዘዴ የተሰበሰበው መረጃ የተሰበሰበበትን መንገድ የተቃና፣ የተሟላ፣ ተገቢውን መንገድ የተከተለ መሆኑን የሚመለከት ነው።

በሌላ መልኩ ከፈተና አኳያ የትክክለኝነትን ምንነት በተመለከተ Heaton (1991) እንደሚገልፁት ትክክለኛነት ማለት አንድ ፈተና የታሰበውን አላማ በሚፈለገው መልኩ ሊለካ የሚችል መሆኑ የሚረጋገጥበት ነው።

የመረጃ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ተግባር ላይ ከሚውሉ የመለኪያ መንገዶች ውስጥ ግልብ፣ ይዘት-ተኮር፣ መስፈርት-ተኮር፣ ትውረት-ተኮር … ተጠቃሽነት አላቸው (ያለው 2009)። በዚህ የጥናት ሂደትም በፈተና አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች የትክክለኛነት ደረጃ ለማረጋገጥ ተግባር ላይ የሚውለው የመለኪያ መንገድ ይዘት-ተኮር ነው። ይህ የመለኪያ መንገድ የተመረጠበት ምክንያት በፈተና አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች በውስጣቸው በሚይዙት ምላሽ አጠቃላይ ይዘት ላይ ስለሚያተኩር ነው።

በመሆኑም የጥናቱን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ለመጠበቅ የተዘጋጀውን ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና የጥናትና ምርምሩ አማካሪና ሌሎች በዚህ የትምህር ዘርፍ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፈተናዎችን ጥያቄዎች ከተለያየ አቅጣጫ ለማስገምገም ከመቻሉ በተጨማሪ አጥኚውም ፈተናዎቹን ሲያዘጋጅ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃና መርሀ-ትምህርቱን መሰረት በማድረግ በድህረ-ምረቃ ትምህርቱ ከተከታተላቸው ትምህርቶች አንዱ በሆነው የፈተና አሰጣጥ ትምህርት (Testing) መሰረት አድርጎ በማዘጋጀት በመጨረሻም ለጥናታዊ ፅሁፉ አማካሪ በማስገምገም በመቅረቡ ውጤታማ ነው የሚል እምነት አሳድሯል።

የተዘጋጁት የመጻፍ ክሂል ፈተናዎች የክፍል ደረጃውን መርሀ-ትምህርት ያገናዘቡ ከመሆናቸው በተጨማሪ ነፃና ጠቋሚ ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ አጭርና ግልጽ ትዕዛዝ ማስተላለፍ የሚመከር በመሆኑ ገላጭና ተራኪ ድርሰቶችን እንዲፅፉ አንዱን ርዕስ በመስጠት ሌላኛውን ደግሞ በመረጡት ርዕስ ዙሪያ እንዲፅፉ እድል ተሰጥቷቸዋል። እንዲፃፉ የሚጠበቁት ድርሰቶችም ለተጠኚዎች ቅርበት ያላቸው ርዕሶች ቢሆኑ የበለጠ የመጻፍ ክሂል ፈተናውን ውጤታማ እንደሚያደርገው በማሰብ ርዕሶችን ላለማወሳሰብ ጥረት ተደረጓል።

ሌላው አከራካሪ የሚሆነው ጉዳይ በቅድመና በድህረ-ትምህርት የሚፈተኑት ፈተና የጥያቄዎቹ መመሳሰልና መለያየት ሲሆን በሁለቱም ጎራ የተለያዩ አስተያየቶች የሚሰጡ ሲሆን ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ግን የተለያየ ጥያቄ ተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልትን በመከተል ጥያቄዎቹ ቀርበዋል።

ለፈተናዎቹ የሚሰጥ ጊዜን በሚመለከት፡- ቅድመ-ትምህርትም ሆነ ድህረ-ትምህርት ፈተናው ሁለት ሁለት ጥያቄዎችን የያዘ በመሆኑ ለቅድመ ትምህርትም ሆነ ለድህረትምህርት ፈተና

ስድሳ ደቂቃ የተሰጠ ሲሆን ይህም የሆነበት ምክንያት በጽሁፉ ላላካተቷቸው ነጥቦች  የሰአት እጥረት ምክንያት እንዳያደርጉ በማሰብ ነው፡፡

## 3.5 የቅድመ እና ድህረ-ትምህርት ፈተና አስተማማኝነት

የቅድመና የድህረ-ትምህርት ፈተና የአስተማማኝነት ደረጃ ለመለካት ለቅድመ-ትምህርት ፈተና የሁለት ክፍል ተማሪዎችን በተራ የእጣ ንሞና ዘዴ በመምረጥ ፈተናው የተሰጠ ሲሆን በፈተናውም ተቀራራቢ ውጤት ያስመዘገቡ በመሆናቸው ሁለቱንም ክፍል በተራ የዕጣ ንሞና አንደኛውን የሙከራ ሌላኛውን ደግሞ የቁጥጥር ቡድን በማድረግ  ለድህረ-ትምህርት ፈተናው የሚያዘጋጃቸውን የመጻፍ ክሂል ትምህርት እንደቅደም ተከተላቸው በሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴና በተለመደው የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተናውን ለመፈተንም ሆነ ሁለቱን የጥናቱን ቡድኖች ለማስተማር በቅድሚያ የትምህርት ቤቱን አስተዳደር ሰራተኞች ፍቃድ በመጠየቅ ፍቃድ ማግኘት  ከተቻለ በኋላ ለቅድመ-ትምህርት ፈተናው የሚሰጠው ሰዓት ለድህረ-ትምህርት ፈተናው ከተሰጠው ሰዓት ጋር እኩል ወይም ተመሳሳይ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ፈታኝ መምህራንም የሚከተሉትን መስፈርቶች በማውጣት መስፈርቶቹን የሚያሟሉ መምህራንን በመምረጥ ፈተናውን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ መስፈርቶቹም፡- ለመፈተን ፈቃደኝነት፣ ተጠኝ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ መገኘት፣ በፈተና ላይ የሚያሳዩት ቁርጠኝነትና የትምህርት ደረጃቸው "ቢ ኤ ዲግሪ"ና በላይ ያላቸው … የሚሉት ሲሆኑ ለቅድመ-ትምህርት ፈተናውና ለድህረ-ትምህርት ፈተናው ሁለት ፈታኝ መምህራንን  በመምረጥ ፈተናው በሰላም ተሰጥቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የፈተናውን ጥራትና የጥናቱን ውጤታማነት ለመጠበቅ ሲባል ነው፡፡ ፈተናዎቹም በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲታረሙ ከተደረገ በኋላ የአራሚዎች የስምምነት ደረጃም በ ክሮንባች አልፋ ተፈትሿል፡፡

## 3.6 የማስተማሪያ ፅሁፍ አዘገጃጀት

ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከቅድመ-ትምህርት ፈተናው በኋላ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎችን ለማስተማር የተዘጋጀው የማስተማሪያ ፅሁፍ በቅድሚያ የአስርኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱትን የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተዳሰዋል፡፡ ይህ ተግባር ደግሞ ለአስርኛ ክፍል ተማሪዎች የሚመጥን ተግባራትን ለማዘጋጀት አመች ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

በ 2007 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ ታትሞ ስራ ላይ በዋለው የአስርኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በስድስት ክፍሎች የተከፋፈሉ የተለያዩ የመፃፍ ክሂል ተግባራት ተካተዋል፡፡ ከተካተቱት አብዛኛዎቹ የመፃፍ ተግባራት በመልመጃ መልክ የቀረቡ ሲሆኑ ትኩረታቸውም ዓረፍተነገሮችን መፃፍ፣ ስለተራኪና ገላጭ ድርሰት ምንነት፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ሴቶች በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያላቸውን ሚና የሚያሳዩ ድርሰቶችን መፃፍ፣ የስራ ደብዳቤ መፃፍ እንዲሁም በስነፅሁፍ ክፍል ውስጥ አንድ ተጨማሪ የስዕላዊ ድርሰት ምንነት … በተመለከተ የቀረቡ ሲሆኑ የተለያዩ ማስታወሻዎችም ተካተውበታል፡፡ የማስተማሪያ ፅሁፉም እነዚሁ ነጥቦች ላይ ያተኩራሉ፡፡

## 3.7 የማስተማር ትግበራ ሂደት

የትምህርቱን አሰጣጥ በተመለከተ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማርና ለመፈተን የሚያስችሉ ለመፃፍ አመች የሆኑ ርዕሶች በአጥኚው፣ በጥናቱ አማካሪና የድህረ-ምሩቃን በሆኑ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካኝነት ተገምግመው የክፍል ደረጃውን መርሀ-ትምህርትና የተጠኝዎችን የክፍል ደረጃ መሰረት ያደረጉ ተራኪና ገላጭ ድርሰቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ፈተና ለቅድመ-ትምህርት ፈተና ተዘጋጅቶ በመስፈርት በተመረጡ መምህራን አማካኝነት ተሰጧል፡፡

በመቀጠልም የቅድመ-ትምህርት ፈተናውን ውጤት መሰረት በማድረግ ተቀራራቢ ውጤት ማስመዝገባቸው ከተረጋገጠ በኋላ በተራ የዕጣ ንሞና አንዱን የቁጥጥር ሌላኛውን የሙከራ ቡድን በማድረግ ለድህረ-ትምህርት ፈተናው የሚያዘጋጅ ትምህርት በአጥኚው አማካኝነት ለቁጥጥር ቡድኑ በተለምዷዊው ለሙከራ ቡድኑ ደግሞ በሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ትምህርቱን ወስደዋል፡፡ ትምህርቱም ለተከታታይ አምስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ክፍለ-ጊዜ በአጠቃላይ ለአስር ክፍለ-ጊዜ የተሰጠ ሲሆን ይህም በተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ ላይ የቀረቡ ይዘቶችን መሰረት ያደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ለማስተማር የወሰደው ሰአትም ቢሆን በመማርያ መፅሀፉ በስድስት ክፍሎች ተከፋፍለው ከቀረቡት አጠቃላይ ተግባራት ከሚፈልጉት ሰአት የሚያንስ አይደለም፡፡ የመማር ማስተማር ሂደቱ የተከናወነው በአጥኚው ቢሆንም ፈተናውን ለመፈተንና በእርማቱ ሂደት የሌሎች መምህራን እርዳታ ታክሎበት ውጤታማ ጥናታዊ ፅሁፍ እንዲሆን የበኩላቸውን ድርሻ ተወጠዋል፡፡

በትምህርቱ ወቅትም የስርአተ-ነጥብ አገልግሎትና አጠቃቀም፣ ርዕስ መምረጥ፣ ርዕስ ማጥበብ፣ መረጃ ማሰባሰብ ማለትም በአእምሯቸው ያለውን ሀሳብ ወደወረቀት ማስፈር፣ አስተዋጽኦ መንደፍ፣ የመጀመሪያ ረቂቅ መፃፍ፣ እንደገና የቀረ ሀሳብ ካለ ደግሞ መፃፍ፣ በንደኛ ማስገምገም፣ ማስታወሻ መያዝ፣ የመጨረሻ ረቂቅ መጻፍ… የሚሉት ነጥቦች ላይ ያተኮረ ሲሆን የትምህርቱ አቀራረብ ግን ተለምዷዊውና ሂደት ተኮር አቀራረብን የተከተለ ነው፡፡

## 3.8 የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ዘዴ

የጥናቱን መላምቶች ለመመለስ ከናሙና ምርጫና ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቀጥሎ ተገቢ የሆነ የመረጃ መተንተኛ ዘዴን መከተል ለጥናቱ ውጤት እጅግ ወሳኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ማለትም በፈተና አማካኝነት አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በቅደም ተከተልና በስርዓት በመደራጀት ጥናቱ በተመረኮዘበት ንድፈ-ሀሳብና የመተንተኛ ስሌቶች መሰረት በማድረግ ተተንትነዋል፡፡ በዚህ ጥናት ለትንተና አገልግሎት ላይ የዋሉት የሁለት ባዕድ ናሙናዎች ጥናት ቲ ቴስትና (Independent Samples T test) እና ዳግም ልኬት ናሙና ቲ ቴስት (Paired observation sample T test) የትንተና ዘዴዎች ናቸው፡፡ ዳግም ልኬት ናሙና ቲ ቴስት መጠቀም ያስፈለገበት ዋነኛው ምክንያት የቁጥጥርም ሆነ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ትምህርት ከመሰጠቱ በፊትና ከተሰጠ በኋላ በአንድ ቡድን ውስጥ የተፈጠረውን የውጤት ልዩነት ለማስተዋል ታስቦ ሲሆን የሁለት ባዕድ ናሙናዎች ቲ ቴስት ለመጠቀም ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ደግሞ በሁለቱ ቡድን መካከል አንደኛው ቡድን ከሌላኛው ቡድን ጋር ያለውን የውጤት መለያየት ለማነጻጸር የሚያስችል እንደሆነ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

## 3.9 የጥናቱ ስነ-ምግባራዊ ሁኔታ

የጥናቱን ስነ-ምግባራዊ ሁኔታ በተመለከተ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድን ይከተላል፡፡ በመሆኑም አጥኚው የሚከተሉትን ተግባራት ለመወጣት ጥረት አድርጓል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ለጥናቱ የተመረጡትን ናሙናዎች ስለጥናቱ አላማ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል፡፡ በግንዛቤ ማስጨበጫ ሂደቱም ተጠኝዎቹ ከመደበኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜያቸው በተጨማሪ ለአምስት ሳምንታት የሚቆይ በሳምንት ሁለት ጊዜ በሃምሳ ደቂቃዎች የተመጠነ በጠቅላላው 10 ክፍለጊዜ የሚቆይ የመፃፍ ክሂልን የተመለከተ

ትምህርት እንደሚማሩ ተገልጾላቸዋል፡፡ እንዲሁም በትምህርቱ ሂደትም ሆነ በፈተናው ወቅት የሚያከናውኗቸው ተግባራት በዋናው የጥናት ውጤት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚፈጥር መሆኑ በአጥኚው ገለፃ ተደርጎላቸዋል፡፡ በመጨረሻም ለጥናቱ ሙሉ ትብብራቸውን ለማሳየት ፍቃደኛ መሆናቸውን እጅ በማውጣትና በጭብጨባ ገልጸው ወደስራ ተገብቷል፡፡ በመሆኑም በእያንዳንዱ በሚፅፏቸው የድርሰት ፈተናዎች ላይ ልዩ መገለጫ እንጅ ስማቸው አይፃፍም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱን የጥናት ውጤት ጥናቱ ለተካሄደበት ትምህርት ቤትና ጥናቱ ለተካሄደበት ወረዳ የትምህርት ፅ/ቤት ለማሳወቅ ታቅዷል፡፡ በዚህ ጊዜ ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ላይ አወንታዊ ውጤት የሚመዘገብበት ከሆነ በሌሎች ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን እንዲሁም ሌሎችን ቋንቋዎች የሚያስተምሩ መምህራን ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብን እንዲከተሉ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይሞከራል ይህ የሚሆነው ግን ጥናቱ ተጠናቆ ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራርያ

### 4.1 የመረጃ አተናተን

የዚህን ጥናት መረጃ ለመተንተን በተሰጠው መላምትና በጥናቱ አላማ ላይ በመመስረት መረጃዎቹ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ መረጃዎቹ ከመተንተናቸው በፊት ግን የሚተነተኑበትን ዘዴ ለመወሰን መሟላት የሚኖርባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ተፈትሸዋል፡፡ ቅድመ-ሁኔታዎቹ ከተፈተሹ በኋላ መረጃዎቹ ተተንትነዋል፡፡ ከትንታኔዎቹ በመነሳት ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ሂደት-ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል በማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና መፈተሽ ሲሆን በውስጡም ዘዴው የመጻፍ ንዑሳን ክሂሎችን ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና ይፈትሻል፡፡

በምዕራፍ ሶስት እንደተገለጸው ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል በካፋ ዞን አዲዮ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ሰባት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዱ በሆነው የሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ 2015 ዓ.ም ትምህርታቸውን በሚከታተሉ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ተተኳሪ የሆኑት ተማሪዎች በቅድመ-ትምህርትና በድህረ-ትምህርት የተፈተኗቸውን የመጻፍ ክሂል ፈተናዎች በሁለት አራሚዎች እንዲታረሙ ከተደረገ በኋላ የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ እንዲፈተሽ ተደርጓል፡፡

#### 4.1.1 የፈተናዎቹ የአስተማማኝነት ደረጃ

የቅድመና የድህረ-ትምህርት ፈተና በመስጠት ውጤቱን መተንተን ከመጀመሩ በፊት የሁለቱ አራሚዎችን የስምምነት ደረጃ መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከዚህ በታች የቀረበው ሠንጠረዥ በቅድመና ድህረ-የመጻፍ ክሂል ፈተና ተማሪዎች ያስመዘገቧቸው ውጤቶች ከአራሚዎች የስምምነት ደረጃ አንጻር አስተማማኝነታቸው ሲፈተሽ የተገኘውን ውጤት ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 1፦ የሁለት ምድብ ተማሪዎች ቅድመና ድህረ-የመጻፍ ክሂል ትምህርት ፈተና የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ (በክሮንባች አልፋ ስሌት)

| ቡድን | የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ |
|---|---|
| የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት | 0.86 |
| የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ትምህርት | 0.89 |
| የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት | 0.86 |
| የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት | 0.9 |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የሁለት ቡድኖች ቅድመ-የመጻፍ ክሂል ትምህርትና ድህረ-የመጻፍ ክሂል ትምህርት ፈተና ውጤት መሰረት በማድረግ ተሰልቶ የተገኘውን የሁለቱ አራሚዎች የስምምነት ደረጃ ያሳያል፡፡ ይህም የአራሚዎች የስምምነት ደረጃ በክሮንባች አልፋ ተሰልቶ ተቀምጧል፡፡ በሁለቱም ቡድኖች አጠቃላይ ቅድመና ድህረ-የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤት የተመዘገቡት የክሮንባች አልፋ ውጤቶች ከ 0.8 በላይ እንደሆኑ ያሳያል፡፡ ይህም የተገኘው ውጤት በሁለቱ አራሚዎች መካከል ያለው የስምምነት ደረጃ አስተማማኝ እንደሆነ መጠቆም ችሏል፡፡

### 4.1.2 የቅድመና የድህረ-ትምህርት ፈተና መረጃ ትንተና

#### 4.1.2.1 በቅድመ-ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የቅድመ-ትምህርት ፈተና ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተሰጠበት ምክንያት የመጻፍ ክሂልን በተለያየ ዘዴ ከመማራቸው በፊት ያላቸውን የውጤት ተቀራራቢነት ለመለካት ታስቦ ሲሆን ለሁለቱም ቡድን ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና መስጠት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት በተለመደው የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ የተማሩ ተማሪዎችና በሂደት-ተኮር አቀራረብ ዘዴ የተማሩ ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ያላቸውን መሻሻል ለማነጻጸርና የሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ውጤታማነት በመመርመር ዘዴው አስተማማኝ ስለመሆኑ መረጃ ለማግኘት ታስቦ ነው፡፡ በመሆኑም

ለቁጥጥር ቡድኑና ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቀን *18/08/15 ዓ.ም* በተመደበው ክፍለ-ጊዜ ቅድመ-ትምህርት ፈተናው ተሰጧቸዋል፡፡ *(አባሪ፡- 7)*

የፈተናውን አስተራረም በሚመለከት ደግሞ መስፈርቱን አሟልተው የተመረጡት ሁለቱ አራሚዎች ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከቃላት አመራረጥና ከስርዓተ-አፃፃፍ አንጻር አርመው የተመዘገበውን ውጤት በመደመር ድምሩንም ለሁለት በማካፈል የተገኘው ውጤት የመጨረሻው አማካይ ውጤት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ *(አባሪ፡- 5*)

የቁጥጥር ቡድን ቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤታቸውንና የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤታቸውን በማነጻጸር ማየት እንደተቻለው በውጤታቸው መካከል የተራራቀ ልዩነት አልነበረም፡፡ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የሁለቱ አራሚዎች አጠቃላይ ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤታቸው (47) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የሁለቱ አራሚዎች አጠቃላይ ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤታቸው (46.39) ነው፡፡ በአጠቃላይ ለሁለቱም ቡድን በተሰጠው ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ለማየት እንደሚቻለው በመካከላቸው ያለው ልዩነት (0.61) ሲሆን ይህም በሁለቱ ቡድን ቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ለመረዳት ያስችላል፡፡

### 4.1.2.2 የድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት መረጃ ትንተና

ለሁለቱም ቡድን የድህረ-ትምህርት ፈተናው ከመሰጠቱ በፊት በይዘት ደረጃ ተመሳሳይ የሆነ ትምህርት በተለያየ አቀራረብ መንገድ ቀርቦላቸዋል፡፡ የትምህርቱን አሰጣጥ በሚመለከት ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በተለምዷዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች ደግሞ በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በአጥኝው አማካኝነት በሳምንት ሁለት ክፍለ-ጊዜ በተከታታይ ለአምስት ሳምንት በአጠቃላይ ለአስር ክፍለ-ጊዜ ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ በቀን 21/09/15 ዓ.ም ድህረ-ትምህርት ፈተናውን ወስደዋል፡፡ (*አባሪ፡- 7)*

የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድርሰቶቻቸውን ከመጻፋቸው በፊት በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የመጻፍ ሂደትን ከማቀድ ጀምሮ እስከ አርትኦት ድረስ ደረጃ በደረጃ የሚቀርብ ሳይሆን ከርዕስ መረጣ ጀምሮ እያንዳንዱ ተግባር በተደጋጋሚ ልምምድ በማርቀቅና በመከለስ ወደፊት ወደኋላ እየተመላለሱ በመጻፍ የተሻለ ድርሰት መጻፍ እንደሚቻል

ባለሙያዎች የገለጹትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ገለጻ ተሰጧቸዋል፡፡

ተጠኝዎችም አንድን ጽሁፍ ለመጻፍ ደረጃ በደረጃ የሚያከናውኑትን ተግባራት መሰረት በማድረግ ሀሳብን በማፍለቅ፣ በማደራጀት፣ በተደጋጋሚ ረቂቅ በመጻፍ፣ በመከለስ፣ ሀሳብን በማደራጀት፣ በአጠቃላይ የተሻለ ይዘት፣ የሀሳብ አደረጃጀት፣የቃላት አመራረጥ፣ የቋንቋ አጠቃቀምና ስርዓተ-አጻጻፍ የሚታይበት ጽሁፍ ለመጻፍ የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል፡፡

የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በድህረ-ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት የሁለቱ አራሚዎች አጠቃላይ አማካይ ውጤታቸው (62.7) ነው፡፡ የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤታቸውና ከቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ጋር ሲነጻጸር የጎላ ልዩነት ማሳየት ችሏል፡፡ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት የሁለቱ አራሚዎች የፈተና አማካኝ ውጤት (46.39) ሲሆን የድህረ-ትምህርት ፈተና የሁለቱ አራሚዎች አማካይ ውጤት ደግሞ (62.7) ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በውጤታቸው መካከል ያለው ልዩነት የጎላ መሆኑን ያሳያል፡፡

ሌላው ተጠኝዎች ለቅድመ-ትምህርት ፈተና የጻፉት ድርሰት ከይዘት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከፊደላት አጣጣል በአጠቃላይ ከስርዓተ-አጻጻፍ፣ ከቃላት አጠቃቀምና ከአደረጃጀት አንጻር ድክመት ተስተውሎባቸዋል፡፡

የሙከራ ቡድን ተማሪዎች (ተጠኝዎች) በክፍል ውስጥ የተማሩትን የሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ስርዓቶችን በመከተል ለድህረ-ትምህርት ፈተና ከጻፏቸው ድርሰቶች ማየት እንደተቻለው በሂደት-ተኮር የአጻጻፍ ዘዴ የመጻፍ ትምህርት ልምምድ ከማድረጋቸው በፊት ከነበራቸው የመጻፍ ክሂል ደረጃ ይልቅ ከትምህርትና ከልምምድ በኋላ በመጻፍ ክሂል አዎንታዊ ለውጥ አሳይተዋል፡፡

የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ለድህረ-ትምህርት ፈተና የጻፉት ድርሰት ከይዘት፣ ከቃላት ምርጫ፣ ከአደረጃጀትና ከስርዓተ-አጻጻፍ ከቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤት አንጻር የተሻለ ለውጥ የታየበት ቢሆንም በቋንቋ አጠቃቀም በኩል በተለይም ከቋንቋው ቅርጽና ሰዋስዋዊ ስርዓት (ሕግጋት) አንጻር ለውጡ ከሌሎች ንዑሳን ክሂሎች ያነሰ ሆኖ ተስተውሏል፡፡ እነዚህ

ንዑሳን የመጻፍ ክሂሎች በሂደት ተኮር የማስተማር ስልት በተማሩ ተማሪዎችና በተለመደው የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በተማሩ ተማሪዎች መካከል የውጤት ልዩነት ተስተውሏል፡፡

ሌላው የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ለድህረ-ትምህርት የጻፉት ድርሰት ከቅድመ-ትምህርት ፈተናቸው ፈተናው ከታረመበት የትኩረት ነጥቦች አንጻር በተወሰነ መልኩ መሻሻል የታየበት ሲሆን ከሙከራ ቡድኑ የድህረ-ትምህርት ፈተና አንጻር ሲታይ ከይዘት፣ ከቃላት ምርጫ፣ ከአደረጃጀት፣ ከስርዓተ-አጻጻፍ ከተጠኝ ቡድን ተማሪዎች አንጻር ድክመት የታየባቸው ቢሆንም በቋንቋ አጠቃቀም በተለይም በቋንቋው ቅርጽና ሰዋስዋዊ ህግጋት በኩል ግን ከሙከራ ቡድኑ የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ *(አባሪ፡- 6)*

በአጠቃላይ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ለድህረ-ትምህርት ፈተና በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተመጠኑና ግልጽነት የሚታይባቸው ይዘቶች በአግባቡ ሰፍረዋል፡፡ በቃላት አጠቃቀም የተሻሉ መደበኛ ቃላትን ለመጠቀም ሞክረዋል፡፡ በቋንቋ አጠቃቀም ረገድም ድርሰቱን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ አገላለጾችን ማለትም የተለያዩ ታሪኮችን በማጣቀስ ሀሳባቸውን አስፍረዋል፡፡ ሥርዓተ አጻጻፍን በተመለከተ ከቅድመ-ትምህርት ፈተናው በተሻለ መንገድ ሥርአተ-ነጥቦችን ተጠቅመዋል፤ ራስጌ፣ ግርጌ እንዲሁም በጽሁፉ መነሻና መድረሻ የወረቀት አጠቃቀማቸውም የተሻለ የሚባል ነው፡፡ ድርሰቶቻቸውም የድርሰት ክፍሎችን ማለትም ርዕስ፣ መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ ያሟላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በቋንቋ አጠቃቀም በኩል በተለይም የዓረፍተነገር ክፍሎችን አሟልቶ ከመጻፍ እንዲሁም የሀረጋት አጠቃቀም፣የመደብ፣ የጾታ፣ የጊዜ አጠቃቀም ወዘተ በተመለከተ መሻሻል መኖሩ የሚካድ ባይሆንም ከሌሎች የመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች አንጻር ሲታይ ግን ይህ ነው የሚባል ለውጥ አልተከሰተም፡፡ እንደአጠቃላይ ግን በድህረ-ትምህርት ፈተናው ውጤት ለማየት እንደተቻለው በሙከራ ቡድን ተማሪዎች ላይ ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል፡፡

## 4.2 የውጤት ትንተና

የሁለቱ ቡድን የድርሰት እርማቱ የተደረገው በድርሰት አቀፍ እርማት ማለትም ከይዘት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከቃላት ምርጫ፣ ከአደረጃጀትና ከስርዓተ-አጻጻፍ አንጻር ነበር፡፡ ለመረጃው አቀራረብና አተናተን ያመች ዘንድ መረጃዎቹ በአራት ክፍሎች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ አቀራረቡም በመጀመሪያ በሁለቱ ምድብ የተመደቡ ናሙናዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለመለየት የቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤታቸውን ማነጻጸር፤ ሁለተኛው የሙከራ ቡድን

ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና ማነጻጸር፤ ሶስተኛው ደግሞ የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ማነጻጸር፤ አራተኛውና የመጨረሻው ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ከሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ጋር በማነጻጸር የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ቀድሞ ከነበረው የመጻፍ ክሂል ደረጃቸው ላይ ያሳዩትን ለውጥ በማየት ስለማስተማሪያ ዘዴው አስተያየት መስጠት ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማም ተማሪዎች በሂደት ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ከተማሩ በኋላ የሚጽፉት ድርሰት ከቅርጽና ከይዘት (ከመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች) አንጻር የተሻለ መሆን አለመሆኑን መፈተሽ የሚል ሲሆን ለዚህም ይውል ዘንድ ዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስትና (Paired Sample T test) የሁለት ባዕድ ናሙናዎች ቲ ቴስት (Independent sample T test) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በምድቦቹ መካከልም የተካሄደው ንጽጽር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.2.1የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በቅድመ-ትምህርት ፈተና የተገኘ ውጤት ትንተና

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመጀመሪያው የትንተናው ክፍል ያተኮረው ቅድመ-ትምህርት ወይም ለጥናቱ የተመረጡት የሁለት ቡድን ተማሪዎች በተለያየ የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት በመጻፍ ክሂል መሰረታዊ ልዩነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው በመፈተሽ ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መረጃው በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

ሰንጠረዥ1፡- የሁለቱን ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት ፈተና የመጻፍ ችሎታ ውጤት ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

| ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ አማካይ |
|---|---|---|---|---|
| የቁጥጥር | 32 | 47.0313 | 8.21872 | 1.453 |
| የሙከራ | 32 | 46.3906 | 7.82442 | 1.383 |

በሰንጠረዥ፡-1 የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ያሳያል፡፡ በሰንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (47.0313) ከሙከራ ቡድን ተማሪዎች

ቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (46.3906) በ (0.6407) በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት (7.824) ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት (8.2187) በ (0.39) አንሶ መጠነኛ ልዩነት ቢኖረውም የሁለቱ ቡድኖች ቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ የማይዋዥቅና የወጥነት ባህርይ የሚታይበት ወይም ተቀራራቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (0.64) እንደበለጠ ለማሳየት ተችሏል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሰንጠረዥ 2 እንደተመለከተው የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ፡-2** የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖች የቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙና | አማካይ | መ.ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የ "ቲ" ዋጋ | ጉልህነት (Sig. 2 tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ | 32 | 47.0313 | 8.21872 | 62 | .319 | .751 |
| የቁጥጥር | 32 | 46.3906 | 7.82442 | | | |

p>0.05

ሠንጠረዥ 2 በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኖች የቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ መረጃው በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱም ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ:- t (62)=-.32, p=(.751) አሳይቷል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከመማራቸው በፊት የነበራቸው የመጻፍ ክሂል ደረጃ መሰረታዊ ልዩነት እንዳልነበራቸው ያሳያል፡፡

### 4.2.2 የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ትንተና

የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ሂደት ተኮር የመጻፍ ትምህርት ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በማሳደግ የሚኖረውን ሚና መፈተሽ ሲሆን መላምቱም ከትምህርቱ በኂላ የመፃፍ ክሂልን በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ

በተማሩ የሙከራ ቡድን ተማሪዎችና በተለምዷዊው የማስተማር ዘዴ በተማሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የመፃፍ ክሂል ልዩነት አለ የሚል ነው፡፡ አላማውን ለማሳካትና መላምቱንም ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 3 እና አራት ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ፡- 3** የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖች ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

| ቡድን<br>Group | ናሙና<br>Sample | አማካይ ውጤት<br>Mean | መደበኛ ልይይት<br>Std. dev. | መደበኛ የአማካይ ስህተት<br>(std. error mean |
|---|---|---|---|---|
| የሙከራ | 32 | 62.7031 | 8.80236 | 1.55605 |
| የቁጥጥር | 32 | 55.8594 | 9.64636 | 1.70525 |

ሠንጠረዥ 3 የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (62.7031) ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (55..8594) በ(6.8437) በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት (8.80236) ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት (9.64636) በ (0.844) አንሶ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጅ የሁለቱም ቡድኖች ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት መጠነኛ ልዩነት የታየበት ቢሆንም ውጤቱ ግን ተቀራራቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና መሰረት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በ (6.8437) እንደበለጠ ለማየት ተችሏል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስን መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ አራት እንደቀረበው የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ፡- 4** የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤቶች ልዩነት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙና | አማካይ | መ. ልይይት | የነጻነት ደረጃ | የ "ቲ" ዋጋ | ጉልህነት (sig 2 tailed) | የ "ቲ" ሠንጠረዥ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ | 32 | 62.7031 | 8.80236 | 62 | -2.965 | 0.004 | |
| የቁጥጥር | 32 | 55.8594 | 9.64636 | | | | |

ሠንጠረዥ 4 በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድን የድህረ-ትምህር የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት መረጃው በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t(62)=3.418, p=.004) አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው በሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በተለመደው የመጻፍ ማስተማርያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በበለጠ የመጻፍ ክሂላቸው ተሻሽሏል፡፡ ከዚህም በመነሳት ሂደት ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ከተለመደው የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በበለጠ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### 4.2.3 የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ንጽጽር

በጥናትና ምርምር ህግ ከልምምድ በፊትና በኋላ የተፈጠረን የውጤት ለውጥ ለመገምገም መጠቀም ከሚገቡን መተንተኛ መንገዶች ዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት አንዱ በመሆኑ ለዚህ ጥናትም አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ይኸውም በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ፡- 5** የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንጽጽር በዳግም ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | አማካይ | መደበኛ ልይይት | ብዛት | መደበኛ የአማካይ ስህተት |
|---|---|---|---|---|
| ቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ | 47.0313 | 8.21872 | 32 | 1.45288 |
| የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ | 55.8594 | 9.64636 | 32 | 1.70525 |
| የሙከራ ቡድኑ ቅድመ | 46.3906 | 7.82442 | 32 | 1.38317 |
| የሙከራ ቡድኑ ድህረ | 62.7031 | 8.80236 | 32 | 1.55605 |

ሠንጠረዥ አምስት ላይ እንደተመለከተው የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸውም የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (47.0313) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (46.3906) ነው፡ በመሆኑም የቁጥጥር ቡድኑ ከሙከራ ቡድን ተማሪዎች በ (0.6407) የሚበልጥ ቢሆንም ልዩነታቸው የጎላ ነው የሚባል አይደለም፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ሲነጻጸር ደግሞ በ (8.8281) በልጦ ተገኝቷል ይህም የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (47.0313) ሲሆን ድህረ-ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት ደግሞ (55.8594) ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በተለመደው የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ የተማሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የውጤት መሻሻል መኖሩን ማስተዋል ተችሏል፡፡

በዚሁ ሠንጠረዥ ሌላው የቀረበው ነጥብ በሙከራ ቡድኑ መካከል በቅድመ-ትምህርትና በድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት የመጣውን ለውጥ የሚያሳይ ነው፡፡ ይኸውም በሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (46.3906) ሲሆን ድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቱ ደግሞ (62.7031) ነው፡፡ በእነዚህ ሁለት አሀዞች መካከል ያለው ልዩነት (16.3125) ሲሆን ይህም በዚህን መጠን ያክል የመጻፍ ክሂላቸው ተሸሽሏል ለማለት ያስችላል፡፡

እንዲሁም በሁለቱ ቡድኖች መካከል በመጻፍ ክሂል ላይ የመጣውን ለውጥ ለማነጻጸር በተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ የተማሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ያስመዘገቡት መሻሻል በአሃዝ ሲገለጽ (8.8281) ሲሆን በሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሩ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በቅድመ-ትምህርት ፈተና ካስመዘገቡት ውጤት በ (16.3125) የመጻፍ ክሂላቸው ተሻሽሏል፡፡ በመሆኑም በተለመደው ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በበለጠ በሂደት-ተኮር የተማሩ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል የሚል ማጠቃለያ ላይ መድረስ እንችላለን፡፡

የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ የአስረኛ ክፍል በካፍኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማሳደግ በተለምዷዊው የማስተማር ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በበለጠ የመፃፍ ክሂል

ችሎታ አላቸው፡፡ የሚለውን የጥናቱ መላምት መልስ አግኝቷል፡፡ በመሆኑም ሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ከተለመደው የማስተማርያ ዘዴ በተሻለ የመጻፍ ክሂልን ያሳድጋል፡፡የሚለው መላምት ተረጋግጧል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የቁጥጥሩንና የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤት በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ጥናት ተደርጓል፡፡

## 4.3 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ፡-

የዚህ ጥናት ትኩረት የጥናቱን አላማ መፈተሽ ሲሆን አላማውን ለመፈተሽም መረጃዎቹ በመጻፍ ክሂል ቅድመ-ትምህርትና ድህረትምህርት ፈተና የተገኙ ውጤቶችን በነጻና በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት በአማካይ ውጤትና በመቶኛ ስሌቶች ተተንትነዋል፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማም ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል የሚኖረውን ሚና መፈተሽ የሚል ሲሆን አላማውንም ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስትና በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡

መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንዳሳየውም በሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በተለመደው የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረ,-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ ልዩነቱ ታይቷል፡፡ ልዩነቱም ጉልህ መሆኑ (በሠንጠረዥ 4) ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ የአስርኛ ክፍል የካፍኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ያለው አስተዋጽኦ ተፈትሾ አወንታዊ ውጤት እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ውጤትም ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ከተለመደው የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ በተለየ ወይም በተሻለ ሁኔታ የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ የሚረዳ ዘዴ መሆኑን አሳይቷል፡፡

ሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ በመጻፍ ክሂል ንዑሳን ክሂሎችን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ በተመለከተም (በሰንጠረዥ 5) ለማየት እንደተቻለው በአራቱ የመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች ማለትም በስርአተ- አጻጻፍ፣ በአደረጃጀት፣ በይዘትና በቃላት አጠቃቀም በሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ የተማሩ ተማሪዎች በተለመደው መንገድ

ከተማሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆን በቋንቋ አጠቃቀም ደግሞ በተለመደው መንገድ የተማሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

ይህም ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ያለውን ጠቃሚነት በተመለከተ የተገኘው የዚህ ጥናት ውጤት Mariam Kadmiry (2021) እና አለምነሽ አሰፋ (2011) በአብዛኛው ተመሳሳይ ውጤት ያሳየ ቢሆንም ንዑሳን ክሂሎችን ባለመተንተኑና የተተነተኑትም የውጤት ልዩነት አሳይቷል፡፡ ለምሳሌ በአለምነሽ ጥናት ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ሁሉንም የመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች እንደሚያሻሽል የሚገልጽ ሲሆን በዚህ ጥናት ደግሞ አራቱን ንዑሳን የመጻፍ ክሂሎች ማለትም አደረጃጀት፣ ይዘት፣ ስርዓተ-አጻጻፍና የቃላት አጠቃቀምን ማሳደግ ሲችል የቋንቋ አጠቃቀምን ግን ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በታች መመዝገቡን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የዳግም ልኬት ናሙናም ሆነ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በሁለቱም ቡድን ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ላይ ጉልህ ልዩነት እንዳለ ያሳያል፡፡ ይህም ልዩነት የመጣው ተጠኝዎች ትምህርታቸውን በማቀድ፣ በማርቀቅ፣ በመከለስና አርትኦት በማድረግ ሂደት በመማራቸው ምክንያት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም ከቁጥጥር ቡድን ድህረ-ትምህርት ፈተና ይልቅ ተጠኝዎች በሂደት-ተኮር አቀራረብ የማስተማሪያ ዘዴ ትምህርታቸውን ከተለማመዱና ከተማሩ በኋላ ለድህረ-ትምህርት የተሻለ ይዘት በጥሩ ቃላትና አደረጃጀት ያሟላ ድርሰት ጽፈዋል፡፡ የሁለቱም ቡድን የድርሰት ፈተናዎች ከታረሙ በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ውጤት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የካፍኛ አፍ-ፈት የአስርኛ ክፍል ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማጎልበት የሚኖረውን አስተዋጽኦ ለመመርመር የተካሄደ ነበር፡፡ ለዚህ ዓላማ መሳካትም በጥናቱ እንዲፈተሽ የቀረበው  መላምት የሚከተለው ነበር፡፡

ከትምህርቱ በኋላ የመፃፍ ክሂልን በሂደት-ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በተለምዷዊው የማስተማር ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የበለጠ የመፃፍ ክሂል ችሎታ አላቸው፡፡

ከላይ የቀረበውን ዓላማና መላምት ለመፈተሽ ጥናቱ በሚከተለው መንገድ ተከናውኗል፡፡

የጥናቱ ስልት በሁለት ቡድኖች ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ከፊል ፍትነታዊ የምርምር ንድፍ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ጥናቱን ለማከናወን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ በካፋ ዞን፣ በአዲዮ ወረዳ፣ ከሚገኙ ሰባት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመች ናሙና ተመርጧል፡፡ በተመረጠው የሜራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ ሶስት የአስርኛ ክፍሎች በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ  ሁለት ክፍል ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡

ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የመጻፍ ክሂል ቅድመና ድህረ-ትምህርት ፈተና ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የመጻፍ ክሂል ፈተና ጥያቄዎቹ በሌሎች የሁለተኛ ዲግሪ የአማርኛ መምህራንና በአማካሪ መምህራን ተገቢነታቸው ተፈትሿል፡፡ የፈተናው ውጤትም የሁለቱ አራሚዎች የስምምነት ደረጃም የአስተማማኝነት መገመቻ ዘዴ በሆነው በክሮንባች አልፋ ተሰልተው አስተማማኝ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

በመቀጠልም የሁለቱም ክፍል (ቡድን) ተማሪዎች ቅድመ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ተፈትነው የተገኙት አማካይ ውጤቶች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልተው በሁለቱ ቡድኖች መካከል የመጻፍ ክሂል ችሎታ ጉልህ ልዩነት ባለመገኘቱ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተብለው በእጣ ናሙና ተመድበዋል፡፡

ከዚያም የማስተማሪያ ይዘቶች ከተለያዩ ጽሁፎች ተመርጠው መማሪያ መጽሀፉን መሰረት በማድረግ ከተዘጋጀ በኋላ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንና ዩኒቨርሲቲ በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገምግመው አገልግሎት ላይ ውለው በሙከራዊ ጥናት ተገቢነታቸው ተፈትሿል፡፡ ቀጥሎም የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ፣ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ በተለመደው የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ለአምስት ሳምንታት ለአስር ክፍለ ጊዜ የመጻፍ ክሂልን ተምረዋል፡፡

በመጨረሻም ሁለቱም ቡድኖች በባለሙያዎች የተገመገሙና በሙከራዊ ጥናት ተገቢነታቸው የተፈተሹ ድህረ-ትምህርት የመጻፍ ክሂል ፈተና ተፈትነዋል፡፡

እነዚህ በፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደ አስፈላጊነቱ በነጻና ዳግም ልኬታ ናሙና ቲ ቴስት ተሰልተው ስታትስቲካዊ ስልቶች አማካይነት ተተንትነዋል፡፡

ከውጤት ትንተናው መረዳት እንደተቻለውም በሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በተለመደው የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ የሆነ ልዩነት አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት ያሳየው ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር ከተለመደው የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅም መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብን ተጠቅሞ የመጻፍ ክሂልን ማስተማር በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ የሚኖረውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱን ትንተናና ውጤት መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ በቋንቋ የመጻፍ ክሂላቸው አማካይ ውጤት በተለመደው የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በተሻለ ሁኔታ ጨምሮ ታይቷል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ

የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማዳበር የላቀ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ከመጻፍ ክሂል ጋር የጠበቀ ቁርኝት እንዳለው ስለሚያሳይ መጻፍን ለማስተማር ተግባር ላይ ቢውልና በስፋት ቢሰራበት መልካም ነው የሚል አንደምታ የሚያሳይ ቢሆንም የቋንቋውን ሰዋስው (ቅርጽ) ለማስተማር ግን ውጤታማ ባለመሆኑ የተሻለው የተለመደው ዘዴ በመሆኑ አልፎ አልፎ እንደይዘቱ ተጨባጭ ሁኔታ የተለመደውን የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴን በመቀላቀል ማስተማሩ አስፈላጊ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡

## 5.3 አስተያየት

የዚህ ጥናት መሰረታዊ መላምቶችና አላማዎቹ ተፈትሸው በጥናቱ የተደረሰባቸውን መደምደሚያዎች ወይም ግኝቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

በዚህ ጥናት ውጤት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ በቋንቋው የመጻፍ ክሂላቸው አማካይ ውጤት ጨምሮ የታየ ቢሆንም ከንዑሳን ክሂሎች አንጻር ባስመዘገቡት አማካይ ውጤት ሲተነተን ግን የቋንቋ አጠቃቀም (በቋንቋው ቅርጽ) ላይ ያስመዘገቡት ውጤት በተለመደው ዘዴ ከተለማመዱት ተማሪዎች አንጻር ዝቅተኛ ቢሆንም በሌሎቹ አራት ንዑሳን የመጻፍ ክሂሎች ግን የተሻለ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ (አባሪ 6) በመሆኑም አራቱን ማለትም፡- አደረጃጀት፣ ይዘት፣ የቃላት አጠቃቀምና ስርዓተ-አጻጻፍን በሂደት ተኮር አቀራረብ ማስተማር ውጤታማ የሚያደርግ ሲሆን የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዐት ለማዳበር ውጤት-ተኮር ዘዴ በመጠቀም ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ስለሚያዳብር ዘዴውን በተመለከተ ለቋንቋው መምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ስልጠና መስጠትና የመጻፍ ተግባራትንም ለዚህ ዘዴ በሚያመች መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

**ይህ ጥናት ትኩረት ያልሰጣቸውንና በስፋት ያልዳሰሳቸውን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የወደፊት የጥናት ጥቆማዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡**

በዚህ ጥናት ውጤት መሰረት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በሂደት-ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ከተማሩ በኋላ በቋንቋው የመጻፍ ክሂላቸው ላይ አተኩሮ በተገኘው የፈተና አማካይ ውጤታቸው በተለመደው የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂላቸው አማካይ የፈተና ውጤት በተሻለ ሁኔታ

ጨምሮ ታይቷል፡፡ ይሁን እንጅ ሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ፍላጎትና ተነሳሽነት ላይ የሚኖረውን ሚና እንዲሁም ንዑሳን የመጻፍ ክሂሎች በስታቲስቲካዊ ዘዴዎች (SPSS) አልተፈተሹም፡፡ በመሆኑም በሌሎች ቀጣይ ጥናቶች የሂደት ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ፣ ፍላጎትና ተነሳሽነት ለማዳበር ያለውን ሚና በተመለከተ እንዲሁም የመጻፍ ክሂል ንዑሳን ክሂሎችን ሌሎች መተንተኛ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ጥልቀት ባለው መንገድ ጥናት አካሂዶ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ዘዴውን በብዙ ናሙናዎች ላይና የማስተማር አተገባበሩንም በሰፊ የጊዜ ገደብ በማከናወን ዘዴው የመጻፍ ክሂልን ለማጎልበት ያለውን ሚና በተመለከተ ቀጣይ ጥናት ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


ማረው አለሙ፡፡ (1996)፡፡ *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሀን ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ሰለሞን ዮሀንስና ሌሎች፡፡ (1994)፡፡ *የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት ስትራቴጅና የመምህራን የማስተማር ተጣጥሞሽ*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አማርኛ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ (*ያልታተመ*)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ *በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡* ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፡፡

አለምነሽ አሰፋ፡፡ (2011)፡፡ *ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴን በመጠቀም ጽሀፈትን ማስተማር የጽሀፈትን ክሂል በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፡፡* ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ አማርኛን ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣(*ያልታተመ*)፡፡

አማረ ተሾመ፡፡ (2010)፡፡ *ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽዕኖ፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ (*ያልታተመ*)፡፡

ዘላለም *መለሰ*፡፡ (2009)፡፡ *የጽሀፈት ማስተማሪያ ስልቶች ምርጫ እና የጽሀፈት ክሂል ተዛምዶ*፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲገሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ (*ያልታተመ*)፡፡

*ያለው* እንዳወቀ፡፡ (2009) *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡.

ዳባሽ ዮሃንስ፡፡ (2011) *በሂደታዊ ዘውግ ማስተማር ዘዴ መጻፍን ለማሻሻል ያለው ሚና*፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ ዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ (*ያልታተመ*)

Ariningish, D. (2010). *The Effectiveness of Using Picture Series To Improve The studentes' Writing Skill Viewed From Their Learning Motivation*. Thesis Submitted For Graduate Degree In English Education Sebelas Maret University.

Bereiter, C. & Scardamalia, M. (1987). *The psychology of Written Composition*. Hillsdale, NJ: L. Eribaum.

Bradly, S. (1994). *Teaching English*. London: Routledge.

Bryne, D. (1988). *Teaching Writing Skills*. Longman: Longman group UK Limited.

________ (1991). Teaching Writing Skills. London: Longman Group Ltd.

Celce Murcia, M. (1991). *Teaching English as ASsecond Language*. Boston: Heinle and Heinle Publishers.

Connor, U. (2002). *New DirectionsIin Contrastive Rhetoric*. TESOL Quarterly, Vol 36 (4), 493-510.

Flower, L. & Hayes, J. R. (1981). *A Cognitiveprocess Theory of Writing*. College Composition and Communication. College Composition and Communication, vol 32, 365 -387.

Grant, N. (1987). *Making The Most of Your Text book*. Hongkong, Longman, Group (FL) Ltd.

Hayland, K. (2003). *Second Language Writing*. Newyork: Cambridge University Press.

Heaton, JB. (1991). *Writing English Language Test*. Newyork: Edinburg Gate.

Hedge, T. (1991). *Writing Oxford*. London, Oxford University Press.

Hillocks, G. J. (1986). *Research on Written Composition*. Urbana.IL National Council of Teachers of English. .

Kaplan, R. B. (1966). Cultural Thought Patterns In Intercultural Communication. Language Learning. Vol 16.

Kroll, B. (1990). *Seconnd Language Writing*. Cambrige, Cambrige University Press.

Leki, L. (1996). *Coaching From The Margins: Issues In Written Response*. Cambridge: Cambridge University Press.

Mariam, K. (2021). *The Comparison Between The Process Oriented Approach and The Product Oriented Approach in Teaching Writing*. The case of

Moroccan EFL. Students in Preparatory Classes for The Grands Ecoles. University of Rabat.

Murray, D. (1982). *Learning by Teaching Selected Articles Writing and Teaching*. Portsmouth: Heinemann.

